http://ethioliberty.wordpress.com/

አውጫጭኝ



ግጥምና

በ

አበራ ለማ

1994/2002




Brought to you by

Ethiopian Bookstore

https://t.me/etbookstore

http://ethioliberty.wordpress.com/



http://ethioliberty.wordpress.com/

የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።

Allrights reserved

Awetsellassie (Dikt samling)
Printed in Norway
Tortatters bokmaskin, 2002

ለደበበ ሰይፉ

http://ethioliberty.wordpress.com/

ማውጫ

ግጥሞች

ትሰስር	7
መልሶ እንዳይነክስህ	8
ይንድ ራስ ንግር	11
እንጃለት	12
እስቲ እንጓዝ	13
እንዲህ ነው	14
ቁራኛ	16
ሰልፍ አስተማሪ	19
ወይኔና ዋኔ	21
መርሃቤቴ	22
ታንኪረኛ ወዳጅ	24
ኧርንጉርጉር	25
እናቱን ጠርጣሪ	27
መድረሻ	30
ቀኚ ብሆን	31
ሰቆቃወ ውስጠት	32
ሁለቱ ሞልታቆች	33
ልጅ እንዳባቱ	34
መለያየት	35
ተስፋ	36
ወዳጅ እልቂ	37
ቱናንትናና አኛ	39
ሞት ነው ዴሞራክራሲ	41
እንዳንተ ማን አለ?	42
አብዬ ፀባይ	43
ይዋሻሉ	46
አሥመሪና	48
ያኔ በልጅነት	49
ሆነ	50

http://ethioliberty.wordpress.com/

እኛ ጫማ ነን 51
እጋዴን 53
ወፍ እንዳገሯ 56
ወደ ምንሳን ዝሆ 57
መንገድ ጠያቂ 59
ያድዋ ትዝታ 60
ያልቀናው ዚቀኛ 61
ጨዋ ከመባል ጀርባ 65
ዝክረ ናይሮቢ 66
መሞት 69
ሰማይና ጣና 70
እግኝ ልብሴ 71
ያ የኛ አበበ 72
የተውነው ቤታችን 73
ባለቅኔዎች 74
የመቀነት ጣጣ 75
ጋዜጠኛው 79
ያልታደለች እልፍኝ 80
እስቲ ትንሽ እንሙት 83
እኔና ልቤ 85
ሊንጋጋ ሲል... 86

ትውፊታዊ ምልልስ

የሴት ነገር 89
የልብ ነገር 95
የእፍ ነገር 98
የወንድ ነገር 100

ትስስር

እንዴት ብዬ_
እንዴት ውጬ_ እንዴት ንጬ_
እንዴት አምጬ_
እንዴት ልውለድሽ?
መቼም መቼም ዝም አልልሽ...
ባታይኝ እያየሁሽ
ባትሰሚኝ እየሰማሁሽ
እንዴት ብዬ_
እንዴት ሁኝ_
ዝም ልበልሽ?
ለዝምታ ልብ_
ለእሽታ አቅም_
መቼም ቢሆን አላደልሽኝ
አልሰጠሽኝ...
እንዴት ብዬ_
እንዴት ሁኝ_
ዝም ዝም ልበልሽ?
እንዴት ብዬ ልተውሽ?

ስንቱን ታምር እያየሁት
ስንቱን ጥበብ እየኖርኩት
ካንቺ ስደርስ _ እንዴት ብዬ
እንዴት ሁኖ _ ልተውሽ?

በጅረትሽ ሳልምልልሽ
በወንዞችሽ ሳልዝትሽ
በተራራሽ ሳልማጠንሽ
እንዴት ብዬ_
እንዴት ሁኝ ልተውሽ?

አዲሳባ _ ግንቦት 1984

መልሶ እንዳይነክስህ

ውሻህን ስትቀጣ
በርህን አትዝጋ

አለ ሃዋርያው ፥ ለደቀ መዝሙሩ
የሚሆነው እንዳይሆን ፥ የመጣ እንደሁ ምሩ!

ምን ያህል ቢወድህ
ምን ያህል ቢሰግድህ
ሁሌም ቢታመንህ
ሁሌም ቢጠብቅህ
መቼም ቢታዘዝህ
ጅራት ቢቆላልህ
ቢንበረከክልህ...
ውሻህን ስትቀጣ
በርህን አትዝጋ...
በሱ እግር ገብተህ
አንተ እንዳትቀጣ...

አለ _ ያ!... ጠቢቡ
ልብ ያለው ከልቡ
ያልጣመው ሰበቡ
ሁዋላ የታየው ስድቡ_

እንስሳ ነውና ፥ ያለአግባብ ቢያጠሩ
ስሜትህ ቢቆጣ ፥ መንፈስህ ቢከፋ
በቅጣት ልታርም ፥ ታጥቀህ ስትነሳ
ውሻህን ስትመታው ፥ በትር ስታነሳ
በሩን ከፈት አርገው
ከውስጥ አታፍንው
አየር አትንፈገው
እንደራስህ አይተህ_
እሱንም ታደገው
ማምለጫ እንዲኖረው
በሩን ገርበብ አርገው!

አለ _ ያ!... ሊቁ ሰው
ንገር ያላማረው
የእምቢይ ካብ እንዲሉ_
መሠረቱን ያባው
ጅምሩ ያልጸዳው!

ንዴትህ እስኪበርድ
ሰውነትህ እስኪርድ
ያላንዳች ይቅርታ
ውሻህን ስትመታ
ምናልባት ቢጎዳ
መሸሽ ካልተቻለው_
ባትሰጠው ቀዳዳ
ዞር ብሎ መንከሱ
ደምህን ማፍሰሱ
መበቀሉ አይቀርም
ከቶም አይተውህም
ምሮም እይምርህም!
እናም... ከፈት አርገው
በርና መስኮቱን
ገርበብ አርገህ ተወው...
አሸክርህ ታዛኝህ_
አንተ ከላይ ሆነህ
እሱ ከበታችህ...
ሲያመው ሲጠናበት
መቋቋም ሲያቅተው
ይሸሽ ሮጠ ይውጣ
እግረ መቅ አታምጣ
ችሎ ማደር በቃው_
ውስጠቱ ተቆጣ

በቃህ በለው አንተም_
በቅቶታል ተቀጣ፤

አለ _ ብልሁ ሰው
ወንፈሱ የታየው_
የታች ታቹን ረግጠ
ውሻን በር ዘግቶ
መቅጣቱ ያልታየው...
ጊዜ ጊዜን ሸሮ
ችሎ ማደር መሮ
አንድ ቀን አይቀርም_
ታች ላዩን መቅጣቱ
ላዩ ከታች ሁኖ_
ወንፈሱን ማግኘቱ፤

አዲሳባ _ የካቲት 1984

http://ethioliberty.wordpress.com/

ያንድ ፡ራስ ንግግር

ተው ሲሉት ቢተው
ውስጥን_
ምናለበት...
ምናለበት ቢተው_
ጥንተ ተፈጥሮ ቢለቅ
ተወኝ ሲሉት ባይጨንቅ_
ምናለበት...
ምናለበት አብሮ ባይኖር_
አብሮ ኑሮ ፥ አብሮ ባይመር፤
ተው ሲሉት ትቶ
ና ሲሉት መጥቶ
እስቲ ምናለበት ቢሰማ_
ውስጥ ሆኖ ውስጥን ከሚያማ፤
ተው ሲሉት ምናለ...
ምናለ ውስጥ ቢሰማ?

ውስጥ አይወጣ
ውስጥን ውስጥ እየዋጠው
ውስጥ እራሱን እየበላ
ውስጥን ውስጥ እየከላ
ተው ሲሉት ቢተው ምናለ?
እንደ ገሞራው እየቀላ
እቶን ቁጣውን እያፈላ
ውስጡን ሁኖ
ውስጥን ከሚቀራ
ተው ሲሉት ቢተው ምናለ_
ውስጥ ውስጡን እየጋለ
ስንቱን ስንቱን...
ስንቱን ጎበዝ አከሰለ!...

አዲሳባ _ ግንቦት 1987

እንጃለት

ቲለው ቲያመጣው_
ማቅ ተመርገምት ቲያለብሰው
አይጣል እንጂ ምን ይሉታል?
የማያድግ ልጅ ቲራገም
የማይሄድ ውሃ ቲወስድ
የማይጥል ዝናብ ቲያበሰብስ_
አጀብ እንጂ ምን ይሉታል
ነሆለል ልጅ ቲያታቅል?

ታባቱ ነው _ ተፈጣሪው
ተናቱ ነው _ ተቆርቋሪው
ተጥንቱ ነው _ ተብቅለቱ
ሸምበቆ ተመሉ _ ዛፍ ቲያክለን
ሲሸመለመል ቲንከባለል _
መቀጫይቱን ቲያስጠቅሰን!
ታያያዝ ቲቀድድ _ ታነጋገር ቲፈረድ
እንዲያ እንጂ ነው _ ተሃች መውረድ?

ተጅምሩ ታሰፋፉ _ ተመጋዱ
ይበየን የለ _ ተምጣዱ
እንጀራው ነፍስ አድኑ...
ምን ባክምባሉ ቢጀቡኑ
ምን በስም ቢያሞነመኑ
የማያጠግበው ይሳሳል ጎኑ
የማያድገው ይድሃል በድኑ!

አዲሳባ _ ሰኔ 19/1983

http://ethioliberty.wordpress.com/

አስቲ እንጓዝ

አስቲ እንጓዝ ፡ እንሸራሸር
እንደ ታይዶንግ እንተማሸር
ሁሉ በኩሰሄ ፡ ምስጢረ ጉባሬን
እንዘምር ተዋደን ፡ ባንሆንም ሁነን!

አስቲ እንሂድ ፡ እንንሸራሸር
እንደ ባህረ ኮራ ፡ እንተማሸር...
ተዚህ መንደር ፡ ተዚያ መንደር እንብቀል
ለብጤያችን እንድንሆን ፡ በአምባችን እንማከል!

አስቲ እንጓዝ ፡ እንንሸራሸር
እንደ ኩምጋንግ ተራራ ፡ እኛም እንደግ
ተውራ ቁንጮነት ተነጥቀን ፡ እንመንደግ!
አስቲ እንጓዝ ፡ እንንሸራሸር
በኩምጋንግ ተመስለን ፡ እንተማሸር!

አስቲ እንጓዝ ፡ እንንሸራሸር
እንደ ኪይሶንግ ፡ ተወጥረን
ባንድ ማእድ ፡ አንኳረፍ
አስቲ እንጓዝ ፡ እንንሸራሸር
እንደ ፒዮንያን ፡ እንመር!
እንደ ታይዶንግ ፡ እንተማሸር!

ፒዮንግያንግ _ ሰኔ 1981

http://ethioliberty.wordpress.com/

እንዲህ ነው

ሩሂቱ ናትና

ለኛ ቢዛይት -

እልፊቱ ናትና

ለኛ ድቀት -

መኖር ነውና

አኝክት -

ዑደት ነውና

ሕልፈት -

እንዲ እንደዋዛ

ሰተት -

ደብቦ ደብቦ

መሸሽ -

እንዲ እንደዋዛ

ቅንጥሽ -

ነበርን ጭልፍ

ደቤን ጥንፍፍ -

በኑባሬ ሕግ

ፕልፍ -

እንዲህ እንደዋዛ

ጭንግፍ -

ደበን

እርግፍ...

አንበሳው ተረታ

ልቡ ሀዘኑን ገታ...

እልፍ

ጭንቡል

ጥቅልል

ብርሃንን - ጥፍት

ጭለማን - ጭውት...

ተለደዘ ሰይፉ
ሳርፕስቦርግ _ ሰኔ 1992

ቁ ራ ኛ

እፍ!... ብስናት ቅርናት
ቅራቅንቦ ማከት
መኛት
ማንቀላፋት...
ማሸተት... ለማቀርሸት
እክ! እንትፍ... ጥልማሞት
ደዌ መሳይ... ግርሻት
ግልማት... እኝካት
እኝካት... ግልማት
ቅራቅንቦ መሻት
ቅራቅንቦ ማከት
መዋተት... መንከራተት
ማስጎባት... ለመጠንባት
ለመጠንባት... ለማስወጣት
እክ! እንትፍ... ለማስወጣት
ለማስወጣት... ለማስጎባት
መቅለሽለሽ ... ማቅለሽለሽ
ለማቅለሽለሽ ... መቅለሽለሽ
ለማኩቱ መዋተት _
መተሻሸት
መገርሻት ... ለተቀርሻት

http://ethioliberty.wordpress.com/

ቁርኝት_
እኝክት_
ዳግም ... ለመተፋት
መጠጣት ... መበላት
ለመዋተት ... ለመተኛት
ቀርንቶ _ ለማቀርናት
በስንቶ _ ለማበስናት...
በጣሪያ ላይ መሰላል ማድራት
በመሰላል ላይ ጣሪያ መሻት
በቁንጣን ላይ ቁንጣን እንዲሉ...
ታዳቆነው ሆኗል ውሉ !

አዲሳባ _ ሚያዝያ 25/82

መንልየ መንልይ ለጊዜው

ሰው አቅሉን አጥቶ፤ ሸፍጥ እያዳጠው
ክርስ እየበላው_
ራስ እየባሰው_
ቤሳ እየዋጠው_
ሚርትን እያጌጠ ፥ ሞትን ሲጠራው
ያኔ ነው _ መጠንቀቅ ፥ ጊዜን ሲበርደው፤
ያኔ ነው መጪንቅ
ውስጥ ራስን መስበቅ፤
ያኔ ነው _ መታመም
ጊዜ ፈት ተነስቶ፥ ሕሊናን መታከም፤

ፍርሃቱን ጋልቦ፤ ሕልሙን እየዋኘ
የዘመናችን ሰው፤ ታች ወርዶ ተገኘ፤
ከሙት ሕልዋን ዘንድ፤ ሕልፈት ከባጃቸው
ልብ እርመኑን አወጣ፤ ልብ አጥቶ ተጃቸው፤

እኒህ ያውሬ ጥፍሮች፤ የሰው ዘር ብስናቶች
ተገዝተው ተሸጠው፤ መኖር የደላቸው...
እኒህ ምናምንቴ፤ ምንትስ ያልናቸው
መንገዳቸው አዘቅት፤ ስውር ኮሽታቸው፤

ልዩ አካሄዳቸው _ አረማመዳቸው
ደሞም አጨባበጥ _ አነካከሳቸው
ተማንም ተማንም... ይልቃል ስልታቸው_
ያንተ ማነህ _ ያቆባዊ ጭውታቸው፤
ልዩ ፍጥርት ያለው _ ሳጥናዔል ሩሃቸው
ዛሬም አደን ላይ ነው _ ሰልቶአል ወጥመዳቸው፤
አንዱን እየዋጡ፤ አንዱን ሲያላምጡ _
አንዱን ማስገራቸው
ባለ እንዲህ ዜማ ነው _ መሪ መዝሙራቸው፤

አዲሳባ _ ታህሣሥ 1987

http://ethioliberty.wordpress.com/

ሰልፍ አስተማሪው

ባለህበት ሂድ አለ_ የሰልፍ አስተማሪ
የሰልፍ ሊቁ መምህሩ...
ግራ እግሩን አንስቶ ጣለው_ ሰልፈኛው
ባለበት ቆመ_ ትእዛዝ ፈጻሚው...
"አልተመታም!... ይመታል!...
ይረገጣል!..." አለ መምህሩ
የሰልፉ ጌታ አባወራ_ ያ ድርጭቱ ያ ኩሩ፤
ዳግም ግራ እግር ተነሳና ተጣለ
አጊራው ጨሰ_ ተጉተለተለ ቦለለ...
"ትም!... ግም!... ድው!..." አለ ሲረገጥ
መምህሩ ዘራፍ አለ_ ጀመረው ሊያፈጥ
እንደ ቲማቲም ሰው ሊያፈርጥ...
"አልተመታም!... ይመታል!...
ይረገጣል!..." አለ ዳግመኛ
ትእዛዝ ፈጸመ። የሰልፍ ተማሪው እግረኛ፤
"ባለህበት ቁም!..." ሲለው ቆመ
ከቀኝ ወደ ግራ ዙር ሲለው ለገመ
"ባለህበት ሂድ!..." ሲለው ተራመደ
"ባላህበት ቁም!..." ሲለው ራደ
ግራ ገባው ሰልፍ አስተማሪ
ምልምል አራቂው ተዶራራ...
ይባስ ብሎ ተማሪ
ተግራ ቀኝ ተጠቀለለ
መሃል ሰፍሮ ዋለለ
ሰልፍ አልገባው ቢል አይፈረድ
ታላያታዝ አይቀደድ
ደሞም እኮ እርጥብ አይነድ...
ቀጠለ ተስፈኛው ሰልፍ አስተማሪ
"ባለህበት ቁም!..." አለው ለያ ተማሪ
"ትም!... ግም!... ድው!..." አለ ድምጹ
"አልተመታም!... ይመታል!...

ይረገጣል!...” አለ ተግሳጹ፤
እንዲህ ያለ ትምህርት
እንዲህ ያለ ሥልጠት
አዲስ ሃዋርያ ካዲስ ደቀመዝሙር
“ቅጥል ቅጥለኒን እንዳሣ ለማስገር
መሬት ይረገጣል፣ መሬት ይታረሳል
ሰልፍ ያላሳመረ፣ ጉድጓዱን ይምሳል”
አለ አያ አስተማሪ_ የማታ የማታ
ልብ አመጽ መግዛቱን_
ተረድቶት ሲረታ፤

ለዳቡሽ
ኢስትሊ _ ሃምሌ 1991

http://ethioliberty.wordpress.com/

ወይኔና ዋ'ኔ

ደረሰ... አምን ጊዜው ደረሰ
“ሃማይ ለሚን ዝፈሰሰ... ”
ከእንግዲህ ወዲህ ከረከሰ
ሌላ ዳንስ ሌላ ጨዋታ ነገሠ...

የሞት ሽታ የሞት ድባብ አጠላ
ወይኔን እየበላ ራሱን እየከላ...
ዘመነ ኦር ጠሩን ሰበቀ
የጎጥ አምባን ጨነቀ
እንግዲህ ጊዜው ደረሰ
ባለሳምንት ተጫጫሰ
የዋ'ኔን ጽዋ ቀመሰ፡፡

እንግዲህ ጎህ ቀደደ
እኩይ ተብጠው ተዋደደ
ወይኔ ዋ'ኔን አጠመደ፤

ኢስትሊ _ ሰኔ 1991

መርሃቤቱ

የድንጋይ ቆጥ _
ቆጥ በቆጥ
በቆጥ ላይ ባጥ _
ባጥ በባጥ
በባጥ ላይ ድጥ _
ድጥ በድጥ
በድጥ ላይ ሰርጥ _
ሰርጥ በሰርጥ
በሰርጥ ላይ ቆጥ _
በቆጥ ላይ አለት
ባለት ላይ ሰማይ _
በሰማይ ላይ ሲሳይ
ተንጠልጥሎ ቻይ
መርሃቤቱ...

በዙማ አፋፍ
ከቆፍና ከፍ
ካጤ ዋሻ ደፍ
ከናዳው አፍ
አልነው አሉ _ ተፍተፍ
ሄድነው አሉ _ እንገፍገፍ
ሆነው አሉ _ ደፍደፍ
ከዙማ አፋፍ
ካጤ ዋሻ አፍ
መርሃቤቱ...

ተድንጋይ ቆጥ
ታለቱ ባጥ
ሌት ስንታትት
ቀን ስንቧጥጥ
ተሸለቆው ተሰርንጕጥ

http://ethioliberty.wordpress.com/

ስናማምጥ_
ስናጋጥጥ
መርሃቤቱ...

ሄድነው አሉ _ በብርኩማ
ዋልነው አሉ _ በቆፍና
ቻልነው አሉ _
ዝለን ደቀን
ካጤ ዋሻ _
ተለጥፈን
ከእናት ጉያ _ ተነፋፍቀን
ልንዋሃድ _ ላብ ተዳፍቀን
ሆነው አሉ _
ሁሉን ሆነን
ሁሉን ችለን_
መርሃቤቱ...

•ለዳንዔል ፋንታ
ዓለም ዙማ _ ግንቦት 1982

ታንኪረኛ ወዳጅ

ግና... ትናንት እንዳለፈ ሁሉ
ዛሬም ያልፋል ሞጋግ ጉመ
የንጹህ ወዳጅ እምባ
የንጹህ ልብ እምምታ
የግፉኃን ጊዜ ሕቅታ
እንደሃች አምናው ጎርፍ
ዛሬም ያልፋል...
የዛሬው ተካኝ፣ አልቃሽ፣ ጎምባሽ
ሳሳህ ይተዋል _ ፍርዱን
ለግዜር ይነግራል _ ውጉን
የኔና ያንቺን...
የየጀችንን
ድርሻችንን
አሳፈ ጠፈ ሞብጣችንን፣
በዘመን ጥላ ተከልሎ
በዱዓ ምኩራብ ተኮፍሶ
በወረት አልማዝ ተንቆጥቁጠ
ወዳጅን እንዲህ ነው _ አልሽ አቀባበር?...
አይ እቱ ቋንጂሊቱ
ድንጋይ ሰባሪቱ
ያኔም ዛሬም...
ጊዜን ዘማሪቱ
ያኔም ዛሬም...
ወረት ኮማሪቱ
ዛሬም ደሞ ...
ነገም ደሞ ያልፋል
ግና ያንቺ
ያንቺ በለስ ግና...
ሁለዜም ያብባል፣

•"ለወዳጆቼ" ቦሌ መንገድ _ 1988

http://ethioliberty.wordpress.com/

ኧርንጉርጉር

ይከፋኛሊ ለምን አይከፋኝ
መጣፉ ሞምር... ሲያቂለኝ
ለምን አይከፋኝ፣ ለምን አይነደኝ?
"ኢትዮጵያዊ መልኩን ነብር ኧርንጉርጉርነቱን
አይለውጥም" እያለኝ
ትልቁ መጣፍ ሞምር ሲያቂለኝ
ለምን አይከፋኝ ለምን አይነደኝ ጎበዝ
የእኔነት አምዱ _ ምሰሶው ሲዝዘገዝ
አዳሚ መቶ ታምሳ መልኩን እያሳየኝ
መጣፉ _ መጣፍ ቅዱሱ ግን... ሃሰት ሲለኝ፣
ዐይኔን ልመን _ ወይስ እሱን
ቀልቤን ልሁን _ ወይስ ጥቅሱን?
ነብሩን ሆነዪ _ ያገሬ ሰው
እ'ስበሱ መልበስ ተሳነው፣
ኧርንጉርጉር _ ኧርንጉርጉርጉር...

ቅድም ሰው _ አሁን አፈር
ጠዋት መልአክ _ ማታ ጋንጩር፣
ትናንት ወጋኝ _ ዛሬ ከሳሽ
አምና አዛኝ _ ከርሞ ነቃሽ_
ሃቻምና አጉራሽ _ ዘንድሮ ነካሽ
ሆነዪ ነብሩን... ያገሬ ሰው
ኧርንጉርጉር _ ኧርንጉርጉርጉር...

ይከፋኛሊ... ለምን አይከፋኝ
መጣፉ ሞምር... ሲያቂለኝ
ባለመሞ ታምሳ መልኩን _ ጠቢያ
አንድ ራሱን... ሲለኝ _ ባምሳያ
መጣፉ... መጣፍ ቅዱሱ
እንደኔ አላየው እሱ...
ኧርንጉርጉር _ ኧርንጉርጉርጉር...

ኢትዮጵያዊነት ባጽመ ቀርቶ
አዲስ ጨዋታ መጥቶ
አዳራሽ ጠቢያ ተውዠርግራ
ሰማንያ ቦታ ተመትራ_
"ኢትዮጵያዊነት መልኩን..." መቼ ሠራ
የሰሚን ቀበሮ _ ተረት ተረቱን እያቅራራ?
ባርባ ልሳን _ ሰማንያ ጎጅ ሠራ
እምቤ ጠቢያን ንዶ _ የባቢሎን መንዲስ ኮራ
ዥንጉርጉር _ ዥንጉርጉርጉር...

ወገኔ... ዥንጉርጉርን ከነብር ቀድቶ
የራሱን ቀለም ለነብር ሰጥቶ_
መልሶ ይስቃል _ በራሱ
ምጸትን አርጎት ምሱ...
እንታይ ዓይነቲ ትራትር _
አብዚ አሎ?
ዋልዳቡን ጋሪ ሚቲ _
አንዲት እናትን ገሎ!
ዥንጉርጉር _ ዥንጉርጉርጉር...

አስትሊ _ መስከረም 1991

http://ethioliberty.wordpress.com/

እናቱን ጠርጣሪ

እቆያለሁ _ እቆያለሁ ጠንቺ
ጥናቱን ይስጥህን ተመርቂ!
አንድ እሷ ብትኖረኝ
አንድ እሷ ብትቀረኝ
አገር ጥዬ ልሄድ_
አገር ለቅቄ ልሰደድ?
አንድ እሷ ብትኖረኝ
አንድ እሷ ብትቀረኝ...
በምን አንጀቴ ችዬ
በምን ጥናቴ ብዬ?
አገር ጥዬ ልሰደድ
ከሰው አፈር ልዋደድ?
በምን አንጀቴ
በምን ልቤ?
እቆያለሁ _
እቆያለሁ እንጂ ተሷው
እምዬም አይዶለች
ቅይምታን ምን አመጣው?
እሞግታለሁ ካንድ ራሴ
ተብሰከሰካ ነፍሴ!

አሳይታ ካልነሳችኝ
እንደ ልጅ ካቀፈችኝ
እንደ እናት ካዋዋችኝ
ተሷ ተእመቤቴቱ _ ተናቴ
ተእትብቴ... ታክላቴ_ ተጉልጥምቴ
ተሷ ሌላ ፥ ተሷ ወዲያማ ማን አለኝ
መንገድ ብሄደው ፥ ብኺትነው_
የእናት ጉያ አይጠብቀኝ!
የለም! የለም እቆያለሁ በርትቺ

በማተቤ ጠንቼ
አንድ እሷ ብትኖረኝ
እንዴት አንድ እሷኑ አጥቼ?
በምን አንጀቴ ችዬው
በምን አቅሜ ጎልብቼው?
አገር ጥዬ ልሰደድ
ከሰው አፈር ልዋደድ?
እሞግታለሁ ካንድ ራሴ
ተብሰክስካ ነፍሴ!

እንዴት ብዬ ልተዋት
እንዴት አድርጌ ሳንቅራት
አንድ አንቺ ነሽ እያልኳት
እያየችኝ _ ስመካባት ፡ ስኮራባት?
የቀትር ጥላ አጥልቶባት
የሰሜን ጋኔን ተጻሯት
ያለ ሁኔትዋ ሲያሆናት
እሷም እንደሰው ሲሻት
እንዴት ብዬ ልተዋት?
እሷ ብተወኝ ፡ እኔ አልተዋት::
አገር ጥዬ ልሰደድ
ከሰው አፈር ልዋደድ?
እሞግታለሁ ካንድ ራሴ
ተብሰክስካ ነፍሴ!

እንዴት ብዬ ልራቃት
እንዴት እምዬን ልጠርጥራት
አንድ እሷ ብትኖረኝ
አንድ እሷ ብትቀረኝ
ቤቴ ጎጆዬ ስላት
ሽቅብ ቁልቁል ደክሜላት
የልጅነት ቅስሜን ፡ ሰብሬላት
እንዴት ብዬ ልተዋት
እሷ ብተወኝ እኔ አልፈጥማት::

http://ethioliberty.wordpress.com/

እሞግታለሁ ካንድ ራሴ
ተብሰክስካ ነፍሴ!
አመዳይ ጠለሸቱን የተቀባ
ባንቺ ወዝ ከደረባ
እንዴት ብለሽ እኔን ትገፊ
ለገፋሽ ጎጠኛ ስተርፊ?
ፍጥርጥርሽን የካደ
አንዲት ጎጆሽን የናደ
እሱ ሲታበይ ባንቺ ጀማ
እውን አላይተሽ እማ
እውን አልሰምተሽ 'ማማ?
አገር ጥዬ ልሰደድ
ከሰው አፈር ልዋደድ?
እሞግታለሁ ካንድ ራሴ
ተብሰክስካ ነፍሴ!
እቆያለሁ _ እቆያለሁ ጠንቼ
ጥናቱን ይስጥህን ተመርቄ!

ለአበራ የማነአብና
ለዶ/ር ታዬ ወ/ሰማያት
አዲሳባ _ መጋቢት 1986

http://ethioliberty.wordpress.com/

መድረሻ

የትየለሌ ነው ፥ ካድማስ ጥግ
ደሞም ቅርብ ነው ፥ ተዚያ አልፎ
ሌላም ጥጋት አለ ፥ በሌላ አድማስ ተጠልፎ
እሱን ማደን ነው ፥ በእጅ ለማኖር
ቅርብ ነው ፥ ቅርብ ለማደር
ሩቁን ማስገር ፥ ናላ እስኪዞር
እዚህ ለማደር_
ሩቅ ማስገር_
ምስጢር ... ምስጢር ... ምስጢር ...
ውስጥን መጫር ... ማጫር ... ማጫጫር ...

ማረፊያ ብጤ ለማቋሮ
መሰንጠር ፥ መሰነጣጠር
ስውር ፥ ሽሽግ ፥ ምስጢር፤
ለሩቅ ቅርበት መዳረሻ
መጠጊያ መሻት መሸሸጊያ
ካድማስ ጥግ ፥ ጭጋግ ጉሙን ገፎ
ሌላም አድማስ ፥ ደሞም እሱን አልፎ
ምስጢር ... ምስጢር ... ምስጢር ...
ውስጥን መጫር ... ማጫር ... ማጫጫር ...

ከቶም!...
ዝም ነው_
ጭጭ አይንቅዝም
እንደ ልባችን አይበልዝም
ብቻ መሄድ ... ብቻ መጓዝ
መንገታገት ... መንገዛገዝ
ምስጢር ... ምስጢር ... ምስጢር ...
ውስጥን መጫር ... ማጫር ... ማጫጫር ...

አዲሳባ _ ጥር 1983

ቀኛ ብሆን

ነገ ሲሆን _
በደመና ግላጭ ፈገግታ
ዛሬ ሲሆን _
በሰማየ ሰማያት አጸድ
ትናንት ሲሆን _
በደመራ ንጫጭ አልባሳት ውጋጌ
ከርሞ ሲሆን _
በቤቴል የጧፍ እምቢልታ ጽጌ
ዘንድሮ ሲሆን _
በምኩራብ ጀንበር ጸዳል ብልጭታ
አምና ሲሆን _
በተስፋ ቀንዲል ወገግታ
እጠቅሳት ነበር _ በምእራፉ
ቃለ ሕይወትን _ ከደጃፉ፤
አጣራት ነበር _ ከሰንኮፉ
ቃለ ሕይወትን _ ከመርገፉ፤
እለያት ነበር _ ከሰፈፉ
ቃለ ሕይወትን _ ከመዳፉ፤
ወለላዋን...
እንዲጠጣው በሰርኑ
መምሰል ሳይሆን _
መሆን ነውና ከሆኑ፤

አዲሳባ _ ጥቅምት 1984

ሰቆቃወ ውስጠት

ዛሬም አለሁ _ አለሁ በድኔን
ያውም ርቃኔን
በድኔን ...

እየበላሁ እየጠጣሁ የሰው ፊት
የሰው ጥርስ
የሰው ነገር
ያን ‘ርሜን...

እየዋለሁ ዓለሜ _ የ‘ልምዓለሙ ሲሮጥ
የ‘ውን ዓለሙ ሲያርጥ
ሁሉ ነገር ሲያጥጥ...
አለየዋለሁ ወገኔ _
ከርሃብ ክፉ ፣ ልባቅልጥ
ከመንገድ ክፉ ፣ ሰርጣሰርጥ
ከሰው ክፉ ፣ ምቅ አምጥ
ካገር ክፉ ፣ ደመና ነጪጥ
እናም አለሁ _ ዛሬም ቁሜያለሁ አካሌ
በሰዋሰው እሽኮለሌ
እየቻልኩት እየዋጥኩት
ያንን ‘ርሜን
የልብ ልብ አመሜን ...
ዛሬም አለሁ _ ሳልነቀል ከፍጥርቴ
ስፋለመው ተኔው አምሳል_
ተጣውንቴ...
ዛሬም አለሁ _ እየሚሚኝ አንኳር ያልኩት
ደቃቅ ልሞኝ _ አሞሌውን ያስጠቀሰኝ
ዛሬም አለሁ _ ውል ጠፍቶብኝ
ከጨው ተራ _ እንዳሰስኩኝ
የማይሚሚ አምጡ እንዳልኩኝ፣
አዲሳባ _ መጋቢት 1987

http://ethioliberty.wordpress.com/

ሁለቱ ሞልቃቆች

የተስፋ ሞላንሞል _ ፍኖት
የወዳደቀች መንደር
የወላቁቀች ጎጆ ፈገግታ
በቀስታ...በለስታ...በጸጥታ...
ድንገት ሲወረወር_
መስኩቲቱ ተከፍታ
የወየቡ ዐይኖች
የተራቡ ጥርሶች
እንዲህ ያፈጣሉ
ጊዜን ይከሳሉ_ በቦግታ
በሽልብታ
ዐይኖች... በብልጭታ
በቁልጭታ
ጥርሶች... እንዲህ ያበራሉ
ይንተገተጋሉ
በመስኩቲቱ ሹልክታ
በሕይወት እራፊ ዛጎታ
ዐይኖችና ጥርሶች
ሁለቱ ሰብቀኞች
እኒህ ምናምንቴ
መድረሻ የለሾች
ሰድበው ለሰዳቢ
ጨዋን ጠቋሚዎች
ገመና ጠቃሾች
ባለቤት የለሾች
በሩ ሲከረቸም
በመስኩት አልቃሾች_
እኒህ ምናምንቴ _ በርሃብ ደናሾች
እኒህ ምናምንቴ
ዐይንና ጥርሶች፣

አዲሳባ _ መጋቢት 1986

ልጅ እንዳባቱ

ምን ብትሸሽ ፡ ምን ብትሮጥ
ሚና ሽንተረር አልፈህ_
ቀለም ብትዘርፍ ፡ መጣፍ ብትገልጥ...
ድምበር ዘለህ ፡ ፊፋ ተራምደህ
ታለህበት ብደርስ...
ያው አንተ ነህ ፡ ያባትህ ልጅ
መልክህ አይገፍ ፡ ግብርህ አይገድፍ፤
አይለቅ የራስ ብጤት
አደተው ክፉ ሚረት
ያውም የጥንት ፡ የናት ያባት
ምን ቢሸሹት ፡ ምን ቢርቁት፤
አስቲ ማን አለ እንዳንተ_
መጠጪኝ ያለ ከማተመ
ልክ እንዳባትህ አንዱን መሻር
አንዱን መሾመ፤
ምን ቢመችህ ፡ ምን ቢከፋህ
ብትሰደድ ባትሰደድ ፡ ምን ሊመጣህ?
ያባባህ ልጅ ነህና ፡
ለምን ያባት ውርስ ይቅርብህ?
ለምን የዘርማንዘሩ ይተደልብህ?
ወንድሞቹ ልመርቅህ ፡ አምን... የዘርህ ያንዘርዝርህ
ለምን ያዳቅንህ... አዝር ቤት ታስሮ ይቅርብህ?

ና'ሮቢ _ መስከረም 1991

http://ethioliberty.wordpress.com/

መለያየት

እል ነበር ... እጠይቅ ነበር _ መለያየትን ፈርቼ
ጨለማን ስሻው ፡ እንዳይለየኝ ሰስቼ፤
እል ነበር ... እጥይቅ ነበር _ መለያየትን ፈርቼ
ብርሃንን ስሻው ፡ ከሌሎች ሁሉ አብልጬ፤
እል ነበር ... እጠይቅ ነበር _
ምነው ጨረቃ ሁሌ አትወጣ?
ምን ይሆን ምስጢሩ ፡ የወር መንፈቁ ሽምጠጣ?
እል ነበር ... እጠይቅ ነበር _ ያቺ በራሪ ኮከብ ተወርውራ
ለምን እደጄ ሁና ፡ ውብ ብርሃኗን አታበራ?
እል ነበር ... እጠይቅ ነበር _ ጸሃይ በከዋክብት ታጅባ
ለምን አላያት መዓልቱን ፡ በመንበረ ንግሷ ተውባ?
እናም እል ነበር ... እጠይቅ ነበር _ መለያየትን ፈርቼ
ያገሬን ሽታ ላልነፈግ _ አድባር አውጋሯን ደጅ ጠንቼ፤
እናም እል ነበር ... እጠይቅ ነበር _ መለያየትን ፈርቼ
ልጆቼን ላልራብ ፡ ደጄን ላልጠግ _ በስደት ታግቼ፤

•ለአቤና ለእንቁ
ና'ሮቢ _ መስከረም 1991

ተስፋ

በለስ ሲቀና
ሃድራ ሲገባ
የነጻነት ቀንዲል
ሲበራ
እውነትም ከቀንም ቀን አለ
የሚያኮራ
በአምላክ እጅ የተሠራ
ከአልማዝ እንቁ የሚያበራ፣
ሕይወቴን ዳግም ልደት
ጎበኛት
የመኖር ሽታ የመኖር ክርቤ
አወዳት
ሃበሻ አብሽ አልሆናት ቢላት
ሰላ ጣእሙ ቢጠፋባት
ባህር ቆርጣ ፡ ድንበር ጥሳ
ከቀንም ቀን አለ ብላ
መሰደዷ ፡ መገፋቷ
ቀን ፈልጋ ፡ ቀን ጠሞባት
የጊዜ ሚርት ተሸርሟት
አልቀረችም አልሞተችም
ሩኋን ስታ
ሕይወት በቀን ተገፍታ
በጊዜ አንደርብ ተመታ፣
ኤሎሂዋን አሰምታ
ሳንድዬ እጇን ሰጥታ
እርይታን ተነፈሰች...
በቀን ውስጥ ቀን አግኝታ፣

ኢስትሊ _ ታህሣሥ 1991

http://ethioliberty.wordpress.com/

ወዳጅ አልቂ

ጥላህን ጥላ _ ጊዜ ይሽረው ዘንድ
አብሮህ ላይንዝ _ መሪር መንገድ
ለምን ይግፋህ _ ተጎኔ አለ ስትል
ንፋስ እንደገለበው ጢስ _ ሲንገዋለል
ለምን ትታመም _ ልተወው ስትችል ትማሰል?

ጥላህን ጥላ _ የዘመን እውልያ ነውና
መምሰልን እንጂ _ መሆንን አይሆንምና፣
አብሮህ ቢውል _ አብሮህ ላያድር
አብሮህ ቢቆይ _ አብሮህ ላይሰምር
አብሮህ ቢኖር _ አብሮህ ላይከትም
የዘመን ጥላ ወዳጅክን _ ለምን ትሸከም?

እሹሩሩ ያልገበት _ ያዘልገበት አንቀልባ
ከሰው ቆዳ የተሠራ _ በሰው ቅስም የደረባ
በሰብእ መንፈስ የተገራ _ በሰው ሩህ የለዘበ
በሰው እምባ የራሰ _ በሰው ፍቅር የደበበ
እጹብ ድንቅ ሥራት ነውና _
እቻ የሌለው በምድር
ለምን ወዳጅ ያልሆነ ጥላህ _
እጅርባህ ታዝሉ ትቸገር?

ወንድምዬ አትታመም _ አውርደህ ላለው ጥላህን
አንቀልባህ ሃቅህ ነውና _ ንጽህናህን ይዘህ አዝግም፣
ወዳጅ ቢሉ ጓደኛ _ የዘመን ሾተላይ ብታይ
የዘመን አረህ አዝመራ _ የጥላ ወጊ ብካይ
ነውና ወንድምዬ _ የጊዜው ልዩ መዝሙር
ላትሸነፍ ተፋሰም _ እጅ መስጠት እንዳይኖር፣

አብሮ ሲያዘግም _ አይታወቅ
ዱካው ሲርቅ _ አይጨነቅ

ጥላ... የዘመን ጥላ እንዲሉ...
ያ ፈተና ያ ፍካት ሲጨልም
ሰብእና ሳሽቆ _ ልበ ሳጥናዔል ሲያገግም
ድብቅ እኔነት ስውር ማንነት ሲያጥጥ
ያኔ ነው መሸሽ _ ያኔ ነው ማምለጥ
እኔነት በሸፍጥ ዋግምት ሲለጠጥ
ወዳጅ እንደ ጥላ ሲያመልጥ
ያኔ ነው ማወቅ _ ያኔ ነው መንቃት
ከራስ ጋር መቅረት _ ከራስ መጫወት፣
ወንድምዬ አትታመም _ አውርደህ ጣለው ጥላህን
አንቀልባህ ሃቅህ ነውና _ ንጽህናህን ይዘህ አዝግም፣

ኢሉቲሲ _ ጥር 1991

http://ethioliberty.wordpress.com/

ትናንትናና እኛ

ለካስ ትናንትም ይሻክራል!...
አሸክላ እንደ በላው ማድጋ
አፈር እንደላሰው ምሳር_
ለካስ የድሮ ድሮ ይጓጉላል!...
ሲሶው ቢጥም ፥ ቀሪው ያማል::

ጨው እንደበላው ቆርቆሮ_
ለካስ የትናንት ዛሬ ያስጠላል!...
ጠባሳው ውርዴ ሁኖ_
ትዝታም እንደ ቁስል ያጣል...
ላይሰሙት፥ ላይዳስሱት፥ ላይጨብጡት
እንደ ሳማ ያቃጥላል፥ ይለበልባል
ለካስ ትናንትም ይሻክራል!...

መጅ አውጥቶ፥ ቡሃ ቆረቆር ሁኖ
የሃቻምናው ልጅነት_
በዛሬው ሰውነት ሲወሳ...
ለካስ ትናንትም ይቆረቁራል!...
በዛሬ እኔነት ላይ ተኝቶ
በዛሬው ትናንት ተድጠ
ያ ዘመን፥ ያ ማሙሽነት ቀርንቶ፣
ለካስ ትናንትም ይሻክራል!...

ለካስ ትናንትም ይመራል!...
ትዝታ እንቆቆ ሁኖ ያቋቁታል
ትናንት ጥላውን ሲያጠላ
ልጅነት የዛሬ ቅስምን ሲበላ
ለካስ አዳሜ ይታመማል...
ትዝታም ሳንጃ ሁኖ ያመማላል
ለካስ ትናንትም ያማል!...

ጅል ከትናንት ራሱ ይጣላል
በዛሬ ሰውነቱ ይማልላል
ለካስ ትናንት ስንቱን ያማል
አንጀት ምሶ ቆሽት አድብኖ
ከልጅነት ጥላ አብንኖ_
ለካስ ትናንት እንዲህ ያማል!...
ለካስ ትናንት እንዲህ ያጣል!...
ወለላው ፈሶ፣ ገፈት አምቡላው ይጠላል፤

ኢስትሊ _ ጥቅምት 1991

http://ethioliberty.wordpress.com/

ሞት ነው ዴሞክራሲ

እውነት የት ነች? እውነት አበባ
በምድር ወይስ በሰማይ _ ለኛ ምትጠባ?
እውነት የት ነች _ እውነት ቀዘባ
በጎነት ወይስ በሲያል _ ተገንዛ ወይስ ተውባ?
እውነት እሊሁ ነች _ እሊሁ ተወልዳ እሊሁ አድጋ
እሊሁ ሸግና እሊሁ ጠውልጋ...

እሷው ነች _ ያቺው የጥንት የጠዋቷ
ብትገረጣ፣ ብትዋብ _ ፍንክች ማትል ከብሔቷ፤
እውነት ነች... እውነት _ ዴሞክራሲም ብንላት
ሃቅነቷ የሚገለጥ _ መቃብር የተማሰለት
ትልቅ ትንሽ ማታውቅ _ ድሃና ሃብታም እማትለይ
እውነት ዴሞክራሲ ናት _ በምድርም ሆነ በሰማይ፤

ጌታና ሎሌን _ መልአክ ሞት የዳኘ ለት
ያኔ ነው ዴሞክራሲ _ እኩይነት ያጠወበት
ሁሉም እኩል _ ጥርኝ አፈሩን የቃመበት፤
እሱ ነው ዴሞክራሲ _ ያ ነው ዴሞክራሲ!...
እቻ መሆን ነግሦ _ የሚረታው ፍራ ክርሲ፤
እኔም አንተም _ በሦስት ሜትር ስንቃደብ
ያኔ ነው እኩልነት _ ትንፋሻችን ስትታገም፤

አስክሬን ሁነን _ የጉዞ ፍታት ሲታደገን
ጎን ለጎን ተኝተን _ እኩል ምስጥ ሲያኝክን
እኔና አንተ ተጣጥመን _ ጥርኝ አፈር ስንጋፈፍ
በእኩል አልጋችን ተንጋለን _ በላይኛው ዓለም ስንሳፈፍ
ያኔ ነው ዴሞክራሲ!... ያኔ ነው ብጹአ ብእጹ
ያኔ ነው ዴሞክራሲ!...

ና ሮቢ _ ጥቅምት 1991

እንዳንተ ማን አለ?

እንዳንተ ማን አለ _
የወደቀ ፍሬ እሚያነሳ
የሰው ልጅ ሲጨቀይ _
እድፉን አጥቦ እሚያነጻ?
ማን አለ? እነ ማን አለ?
ካንተ ሌላ _ ለኔ ብጤው የዋለ
ማን አለ? እምዬ ናት አልል
ከእምባ ግብር ሌላ አትከፍል፣

ስደቴን ሳስታምመው _ መከራዬ ሲበረታ
ዋስ ስጠራህ የቆምክልኝ _ የክፉ ቀናቴ ጎለጎታ፣
አሁን እንዳንተ ማን ደግ አለ
ለለመነው ፣ ለተማጸነው በተጠራበት የዋለ?

እንደ ሰው ልብ ያልሻከርክ
ጥንትም የነበርክ
ዘለዓለማዊ አርኬ
አንተው ብቻ ነህ!... አምላኬ።

ለመንገሻና ለአልማ
ና'ሮቢ _ ታንዛኒያ 1991

http://ethioliberty.wordpress.com/

አብዬ ዐባይ

አንቺው ታመጪው ፣ አንቺው ታሮጪው እንዲሉ
ማደሪያ የለህ... ስንለው፣ ኪላ ሰብሮ መኮብለሉ
ማያንሰው እንጂ ፣ መች ላመሉ
አብዬ ዐባይ ቢክፋው
ሲታን አላይ ብለነው
ሲጠራን ዳባ ብለነው
ርቦን አልበላነው
ጠምቶን አልጠጣነው
በርዶን አለበስነው
ምነው አይከፋው አብዬ
ምነው አይከዳን አንድዬ
ሞረሽ በሉ! እሪ በሉ!...
ዘራፍ በሉ! ጎበዝ በሉ!...

አንተ የካም ፣ የኩሽ ትክል
የሴም አምባ ፣ የግዮን ሽል
አብዬ ዐባይ ፣ ያፍሪካ ቀንድ
የእምዬ ልጅ ፣ የታሪክ አምድ
የእኛ ሳያንስ ፣ አንተም ደሞ ልትሰደድ?
አንተም? አንተም ደሞ እንደሌላ
ጦር ልታስጭን ፣ ጉድ ሊፈላ?
አንተም ደሞ ጨከንክብን
ከዘመኑ ተሸርጠህ ፣ አደምክብን?
አብዬ ዐባይ ፣ ጦር ላክብን?

እንግዲህማ ማን አለን
ስማችን ምልክታችን ከሄድክብን
እንግዲህማ ማን አለን?
የማናችሁ ሲሉን ፣ የማነን እንበል
ደሞስ ደሞ ፣ ባንተ ጦስ እንማሰል?
ነደን ነደን እንከሰል?

ከስለን ከስለን እንቅስል?
ኧረ ተው ዐባይ ታረቀን
ውሾን ያነሳ ውሾ አትበለን፤
ሞረሽ እንበል! አሪ እንበል!...
ዘራፍ እንበል! ጎበዝ እንበል!...

አብዬ ዐባይ ፥ አንተም ጨክንክብን
ከዘመኑ አዚም ገጠምክብን?
ካያያዝ ይቀደዳልን ተረትክብን?
እምዬ አቅሚ ቢደክም ፥ ልጆቿም ባንረባት
አያያዝዋን አይቶ ሞብጠዋን ሊቀማት
አሾተሰብን ? ሰንጋ መጢቃ
ባንዳ ተክሰብን ፥ አንቃ ላንቃ
ለክፉ ቀን አይበቃ...
ማን ይሁነን ጋሻ ፥ ማን ይሁነን ጠበቃ?
"ዐባይ ለያእቆብ ፥ ዐባይ ለየሱፍ ምኑ ነው?"
የሚል ሃሳዊ መሲህ ፥ በዘመናችን ነግሦ
ቢያበላን ጠርነት ፥ ቢያጠጣንም ክሰ፤
የዛር ውላጅ ይመስል ፥ ደም ላይ ተጎንብሶ
ይኸው ያምሰናል ፥ ክፉ ቀን ደግሶ፤
መለስ ብለን ሰማን ፥ ዜናዊ ተረት
ዐባይ ፀሐይ በላው ፥ የእምዬን ፍትፍት፤
እግዚኦ በሉ! ሞረሽ በሉ!...
አሪ በሉ! ዘራፍ በሉ!...

እባክህ ተማለደን ፥ እባክህ ታረቀን አብዬ
ባንተ መዘዝ ላንፈጠም ፥ ቃል ማባላት ለእምዬ፤
ጌታና ሉሌ ተጣልተው
ዱባና ቅል ተማተው
ውሃና እሳት ተጋብተው
ኧረ አይሆንም ተው!...
ተው ስልህ አብዬ... ዐብዬ ያገር ማተም ፥ ያገር ድጉ
ያገር ጌጡ ፥ ያገር አዋይ ፥ የባላገሬው ወጉ፤
ስትገማሸር_ ስትንፏለል_ ስትገማሸር...

http://ethioliberty.wordpress.com/

አቀብ ቁልቁል ስትማስን ፥ ስትንከላወስ አገር ላገር...
እዝማሪው ከራር አከሮ፤ መሰንቆ ከርክሮ
በገና ደርድሮ ዋሽንቱን ኮርኩሮ_
ሠዓሊው ብራና ፍቆ ሸራ ወጥሮ ቀለም ቀይጦ
ባለቅኔው ውስጡን አንቅቶ መዲና ዘለሰኛውን አምጦ
እዜመሀ ኪለሀ ተቀኝሀ_
ያን ሁሉ አጀብ ዘመን...
አንተ ግን "እናንተም ለያቸሁኝ ከደረት
ጸሄም አየኋቸሁ ከጉልበት"
ሳይሆን አልቀረምና ጥሉ
ኧረ ጎበዝ መላ በሉ!...
ልጅ ባቦካው ከምንቆላ
ሳንበላ ከምንበላ
ላብዬ ዐባይ ስጡት መላ፤

ያባይ ነገር የኛ ነገር
'አምራና ቅል ተጋቡ
አሞራው በረረ
ቅሉ ተሰበረ
እንዳይሆን ውሉ ካደረ...

•ለየሱፍ ያሲንና ለያዕቆብ አርዛኖ
ሳርፕስቦርግ _ ታኅሣሥ 1993

ይዋሻሉ

አትመናቸው _ ይዋሻሉ
ሳይስቁ ስቀው _ ያስቃሉ
አትመናቸው _ ይዋሻሉ
ሳያዝኑ አዝነው _ ያስለቅሳሉ
አትመናቸው
ይዋሻሉ...
እየበሉ _ ይራባሉ
እየጠጡ _ ይጠማቁ
አትመናቸው
ይዋሻሉ...
አደግድገው _ ያድራሉ
እግር አጥበው _ ይሰማሉ
አትመናቸው _ ይቀጥፋሉ
አትመናቸው
ይዋሻሉ...
እየሞቱ _ ይኖራሉ
አትመናቸው _ ይዋሻሉ
ተሸንፈው _ ያቅራራሉ
አትመናቸው
ይዋሻሉ...
እንዳውሬ _ ይኖራሉ
አትመናቸው _ ይዋሻሉ
እንደሰዎች ያልፋሉ...
አትመናቸው _ ይዋሻሉ
እንደ ሸምበቆ _ ያድጋሉ
አትመናቸው _ ይዋሻሉ
እንደ ባቢሎን ይናዳሉ...
አትመናቸው
ይዋሻሉ...
ነፍስ ዘርተው _ ያጭዳሉ
አትመናቸው _ ይዋሻሉ

http://ethioliberty.wordpress.com/

የሞቱትን _ ይተፋሉ
አትመናቸው _ ይዋሻሉ
የሰቀሉትን _ ያወርዳሉ
አትመናቸው _ ይዋሻሉ
ያወረዱትን _ ይሰቅላሉ
አትመናቸው
ይዋሻሉ...

አዲሳባ _ ሕዳር 1984

አሥመሪና

አሥመሪና... አየሁሽ እቴ
አየሁሽ _ ደጃፍ ተቀምጠሽ
አመሻሽ ላይ_
የምሽት ጨረቃን እንደሚናፍቅ ሕጻን
የደመነውን ሰማይ ስትማልጂ...

አየሁሽ _ ኩርምት ብለሽ ተጨብጠሽ
አባወራዋ እደጅ እንደቀረባት እመቤት
አየሁሽ እቴ _ አሥመሪና
እንግዳሽ ሁኔ ተጎዳና
ስቀሽ አላስቅ ብለሽኝ
አላሽኮረምም አላስቀና...

አየሁሽ አሥመሪና
አየሁሽ _ ደጃፍ ተቀምጠሽ
እንደበረዶ ቀዝቅዘሽ
እንዳምሉ ደመና ክብደሽ
እንደናሴ ሰማይ ጠቁረሽ
አየሁሽ እቴ ተጀቧቡነሽ...

አየሁሽ አሥመሪና
ያ ገጥታሽ ወይቦ
ፊትሽን ማድያት ወርሶት
ጥንተ እኔነቱን ተርቦ
አየሁሽ _ አሥመሪና
እንቲ ሃፍቲይ _ ሃፍቲይና
እንቲ ጓልቲ _ ጓል ጓልና
እንቲ አሥመራ _ አሥመሪና
ያደዱ ልጅ _ ሾኮሪና...

አሥመራ _ ነሃሴ 1980

http://ethioliberty.wordpress.com/

ያኔ በልጅነት

ነጋ አልነጋ
የኩኩሉን ድምጽ ጠብቄ
በላምባዲና ዐይኔን ጨምቄ
ጥናት ይሉትን ሳነጋግር
በውድቅት ሌሊት ሳጓጕር
ነጋ አልነጋ
አፌን በእፍኝ ቆሎ አሟሽቼ
ደብተሮቼን እብብቴ ሸጪ
ከጎደኞቼ ተያይዤ...
አቀበት ወጥተን _ ቁልቁለት ወርደን
መጫሚያ አልባ ኑረን
እንቅፋቱ ሲያነግለን_
የማለዳ ቁር ሳይበግረን
የጠዋት ጤዛ ሳያግደን
እኾሀ ቆንጥሩን ረምርመን
እንበር ነበር ... ወደ ቀሰም_
ነጋ አልነጋ
ከተማሪ ቤት ደርሰን
በየፊናችን ተዘርተን
የልባችንን ተጫውተን
የደወል ድምጽ ጠብቀን
የጠዋት ጸሎት አድርሰን
ሰንደቅ ዓላማን ከበን
ሰንደቅ አላማቾቻን ዘምረን
ባንዲራ አውጥተን
ለጠቢያችን ቃል ገብተን _
ነጋ አልነጋ
እንዲህ ጸንተን _
እንዲህ አምረን
ያኔ... ያኔ ልጆች ሁነን...

አዲሳባ _ መስከረም 1970

ሆነ

ሄድነ _ እየተከደነ
ጠፈር እየዳሰነ
ሄድነ _ እንደተሸፈነ
ሳንገት ልብስ የለነ
ባየር ተንጋለነ
ተኛነ _ እንደተነገርነ
ከቶም አልቃዠነ
ጠጣነ _ እንዳልተጠማነ
በላነ _ እጅ እንደሰጠነ
ሸመትነ _ እንደተመራነ
ሱቅም አልመረጥነ
ከፈልነ _ እንደተጠየቅነ
አልተከራከርነ
ተማርነ _ ቋንቋንም አወቅነ
ሳምሳሚዳም አልነ
ስልሳ ሚዳም አልነ
ሰባንም ደገምነ
ጨፈርነ _ እንደተከደነ
ደነስነ _ ጠቢያን ሸተትነ
ኮራነ _ ኮርዮን መሰልነ
ፈሰትነ _ ፋሲካ ሆነ
መጣነ _ አንድም አልጎደልነ
ሕመም አላየነ
ሞት አልጎበኘነ
እጅም አልሰጠነ፤

ፒዮንያን _ ሰኔ 1981

http://ethioliberty.wordpress.com/

እኛ ጫማ ነን

እኛ ጫማ ነን_ ወደር የሌለን
ወጪ ወራጁ ሲጫማን_
ሰጥ ለጥ ብለን የታዘዝን
እኛ ጫማ ነን_
ሸክሙ በዛብን ያላልን
ሁሉን ቻይ ጌታ_
ባምሳሉ ቀርጾ ያኖረን
እኛ ጫማ ነን _ ጫማ ሁነን
የጫማ ዘር መዝራታችን
ምስክር ነው _ ለእኛነታችን፤

ባለጊዜ በፈረቃ ሲጋልበን
ቺ ፈረስ ... ሲለን ሲንጠን
እንደ ስናር በቅሎ ሲያሰግረን
እኛ ጫማ ነን_
ሁሉን ችለን _ ሁሉን ውጠን
ዳገት ቁልቁለት _ ደጋ ቆላ
ምን እቻ አለን _ ስንፎገላ?

እኛ ጫማ ነን _ ወደር የሌለን
እንኪን ሰው ጊዜ ዞሮብን
እያነሳ የሚጥለን መብዛቱ
ያልሞከረን ያልተጫማን መታጣቱ
እቻዮ ዲፈሮ መባላችን
የማንታሽ የማንቆረጠም_
የብረት ቆሎ መሆናችን
ምስክር ነው _ ለእኛነታችን
ጫማ ሁነን _
የጫማ ዘር መዝራታችን፤

ስንረገጥ ስንፎክት መቻላችን

ምስክር ነው _ ለእኛነታችን፤
ግና... ግና ነው ጉልበታችን
እንዱ ጥሉን _ ሌላው አንስቶ ሲጫማን
በቃን አለቅን ነተብን የማንል
እኛ ጫማ ነን _ የእምዬን እኖ የምንከፍል፤

እንደ ሰም ቀልጠን እንደ ብረት ተቀጥቅጠን
የወርቅ አምባር ያልማዝ ጉትቻ_
ቀለበት ሃብሉ ሁነን
ስንቱን ስንቱን ባለጊዜ_
አሳምረን እንቆጥቁጠን
ሳያልፍልን አሳልፈን_
ሽሮ ሳናይ ፌጫማ አብልተን
ቅራሪ ሳናይ _ ውስኪ ጠጁን አስጎንጭተን
ጎጆ ብርቁ እየተባልን _
እልፍኝ ካዳራሽ አስመርጠን
እኛ ጫማ ነን _ ሁሉን የቻልን
ጫማ ሁነን _ የጫማ ዘር ማዝመሩ
እንዲህ ተናኝቶ ባገር ምድሩ
እግዚኦ በበጊዜሃን መዘመሩ
ይኸው ነው _ ለእኛነታችን ምስክሩ፤

ሁሉን ችለን _ ሁሉን ውጠን ያሳለፍን
እኛ ጫማ ነን _ ወደር አቻ ያልተቸረን
እኛ ጫማ ነን _ ካንድዬ ሌላ
ማንም ምንም የሌለን፤

ለንጉሴና ሲሳይ ታፈሰ
ኢስትሊ _ መጋቢት 1992

http://ethioliberty.wordpress.com/

አጋዴን

ግመሌ ... ገስግሽ ርምጃሽ ይፍጠን
ከዚያች መንደር ገብቶን ማደር አለብን
አቅጣጫሽም አቅጣጫዬ ነውና_ ልከተልሽ...

ግመሌ ምሪኝ_ አድማስ የለሹን ወሰን አሳይኝ
የአጋዴንን በረሃ ዝና ፣ በክፉ ጎኑ ቢያስጠኑኝ
አሸዋው ውጠ እንደሚያስቀር ፣ አሟራው እንደሚያፍነኝ
በቀልዱም በምሩም ቢያወጉኝ
ግና... አጋዴን መች ለኔ ጀርባ ሰጠኝ
አይወብቀኝ_ አይደክመኝ_ አይጠማኝ_ አይርበኝ
ይልቅስ ወኔዬ እንደበረታ እንደታጠረ
ዐይኔ ማዶውን እንዳማተረ...

ግመሌ ... ብቻ ቅደሚልኝ_ ጉዞዬ ረጅም መሆኑን አስቢ
እንደ በቅሎ ስገሪ ፣ እንደ ፈረስ ሽምጥ ጋልቢ!...
አጋዴን እንደጎመ እንደጨጓጣ ፣ ሃሩር አርግዞ ይታየኛል
ኩራዝ አይሉት ፋኖስ ፣ ሌትና ቀን ይንጨለጨላል
ግመሌ አስቢልኝ... እኮ በይ ጀግኖች አምላ ድረሽልኝ
ቀብሪ ደሃርን፣ ደገሃቡርን፣ ዋርዴርን፣ ቀላፎን፣
ጎዴን፣ ወልወልን አሳይኝ
ደሞስ ግመሌ ይታይሻል?... ያ ኤላ አጀብ ስዩ አጀብ ጎጥ-ቆ
ብጤዎችሽ ተሰብስበው፣ የጋማ ከብቱ፣
ፍየሉ፣ በጉ ተጠራርቶ
ከዚያ ቅንጥብ ከዚያ ግርግድ_ ሆድ ተሞልቶ...
አሪያ በጀለቢያ ጉንጽፍ ተሸልሞ
ግመሌ ... የጋማና የቀንድ ከብቱ በጅር ተሞ
ዐየሽ ልብ አልሽው... በዚህ ምሽት
እዚያ ማዶ ሚፍ ሲበራ
ከመጅሊስ ዙሪያ እጣን ሰንደሉ መንገደኛን ሲጣራ?
ግመሌ... አጋዴን መድረሻ የለው መሰኻ
ሲቀርቡት ይርቃል፣ ሲርቁት ይቀርባል_ አጉል ሆደ ባሻ፤

ግመሉ... ብዙ ባይደንቅሽ ብዙ ባይገርምሽ
እኔ እንግዳ ነኝ ለመንደርሽ
አባቴ ነበር ያደገብሽ፣ የኖረብሽ፣ የሞተብሽ
እና... ለኔ እሚታየኝ ይታይሽ ይሆን ሳንቺም
የአጋዴን ፍጥርጥሩ፣ ነገረ ሥራው ሲታሸም?
አየሽ ግመሉ... ሕይወት አንዳንዴ ጠውልጋ፣
ስልምልም ስትል አይገባ
እንዱ ሲተኛ እንዱ ሲነጉድ፣ በጠፍ ጨረቃ
ገሚሱ ሲቃፍር፣ ገሚሱ ሰርጎ ሲያጠቃ
ታዲያስ አጋዴን እንደምነው ስታውቂው
ግልገል ሳለሽ ውርንጫ፣ ጎልማሳ ሳለሽ መሮጫ?

ካሸዋ ዳክረሽ_ ቆንጮር ግራሩን ጥሰሽ
በዚያ በረሃ በዚያ ሃሩር ተጠብሰሽ
ኤላ ፍለጋ አገር ምድሩን ባዝነሽ
ምን ታዘብሽ? ምን አስተዋልሽ በውስጠትሽ
የሰም ኩሹን ምድረ ሳባ ጋልበሽ አልፈሽ?
እኮ አጋዴን የማን ነበር? ዛሬስ የማነው ተናገሪ
ያየ ይናገር፣ የቀበረ ያርዳ ነውና... ግመሉ መስክሪ!...
መስክሪ ግመሉ፣ እውነት ተናገሪ
ያባቱን ሳያውቅ፣ አያት ናፈቀን ሩጫ ስበሪ
አባቴ እንጂ ሌላ አይደለም_ አብሮሽ የኖረ
አሸዋ ለብሶ፣ ኮዳ ተንተርሶ_ በእርሳስ አረር ያረረ...

እኮ ግመሉ... አቅጣጫዬን አሳይኝ
ወደ እዚያች መንደር ምሪኝ
ኮርሽ ይንቃጨል፣ ዱካሽ ይታየኝ
ከደገሃቡር ቀብሪ ደሃር አድርሺኝ
ፍሬ ካበባ ቢገኝ አፋልጊኝ
ከዚያች ጎጆ ከዚያች መንደር አጨባብጪኝ
ለጋ ሕይወት እምቡጥ ፍሬ
ወድቆ አይቀርም፣ ትናንት ዛሬ፣
እኮ ግመሉ... ስገሪልኝ ገስግሺልኝ

http://ethioliberty.wordpress.com/

ትዝታ አልባ እንዳልቀር፣ ቀብሪ ደሃርን አሳይኝ።
እኔ ስጨነቅ፣ ደቂቃው ሰዓት ሆኖብኝ
ቀኑ በወራት ተመንዝሮ፣ ርሃብ ጥማቱ ሳይበግረኝ
ለምን ታዘግሚያለሽ፣ ተራመጅ እንጂ ፍጠኝ
ገና ወልወል ደራሽ ነኝ፣ ቀላፎ ላይም ጉዳይ አለኝ።
ግመሉ... ውሃ ስንቁ ነሽ ሲሉኝ፣ ሲያስተዋውቁኝ
የኦርያው ሁለመናው አንቺ እንደሆንሽ ሲያጫውቱኝ
እጅርባሽ ታዝዬ፣ አየሁት ሁሉንም፣

አሪያ ዊልኩን ይዞ፣ ወተትሽን በየሰንቱ ሲያንጥሩ
በውልውሉው ሲመትርሽ፣ እሱ ከነገር አንቺን ሲያከንፉ
አንዴም ዞሮ_ በሂና ተኩሎ፣ ተሟለትልቶ
ኩሉምባውን ሬት ነሰቶ፣ ከራሱ ላይ አውልቶ
ኮጯውን ተጫምቶ፣ ያንን አሸዋ ሲያረግድ
አንቺ ግን ሻባቲ አልባ፣ አብረን ስንኑድ
አየሽ ግመሉ... አጋዴን ገና ጠብ አላለልንም
ጎጇችን ያች ጉርጓችን አትታየንም
አየሽ ግመሉ... አጋዴን መነሻ የለው መድረሻ
ሲቀርቡት ይሸሻል፣ ሲርቁት ይቀርባል፣ አጉል ሆደ ባሻ፣
ግመሉ... አንቺ ሰጋሬ፣ አንቺ በቅሎዬ
ዋርዴር ደገሃቡር ጎዴን አዳርሺ፣ ቀብሪ ደሃር ነው ሚሄሪያዬ
አንድ ነው መንገዴ_ ይኸው ነው ምርጫዬ...
መንገድሽን እንዳትስቺ፣ ኮርሽ ይንቃጨል ትንሹ ደወል
ቅፍለት ያለፈበትን ያንን ዱካ እንከተል፣

አጋዴን ምድራችን፣ ታሪክ ያስታውሳል
አባቱን የማያውቅ አያት እንዳይከድል
እንኳን ተስፋፊውን፣ አፈንጋጩን ያማል
ግመሉ መስክሪ ሃቁን ተናገሪ
መንገድሽን አትርሺ ገስግሺ ብረሪ
ሟፍ ከሚበራበት ከዚያች መንደር ገብተሽ ሌሊቱን እደሪ
አይሆሽ ጠና በይ... በርቺ ተራመጂ!... ግመሉ ጠንክሪ!...

(ዋርዴር _ ጥር 1971)

ወፍ እንዳገሯ

ወፍ እንዳገሯ_
እንዳገሯ ትጨህ
እንደ ቆሌዋ ታቅራራ
ደብር አስተኔ ቅኔ ዘምራ
ወፍ እንዳገሯ
እንዳገሯ ታቅራራ
እንደ ብጤቷ እንደ ሁነቷ
ትሞዝቀው ታንጎራጉር ለብሶቷ
ወይ ትጨፍር ትረግጠው ያን ዳንኪራ
ወፈት እርግብግቢት፥ እንዳገር እንደ መንደሯ
ትርገፈገፍ ትሽከረከር ለብጤትዋ
ወፍ እንዳገሯ እንደቤትዋ
እዚም እዚያም ነውና ሃሴት
ውስጥን ማድመጥ ለመላመድ
ወይ ለመሄድ ወይ ለመዳህ
ሕይወት እንዲያ ነችና ስትመላ
ስትሠራ ስትከሸን ስትኮላ
ወፍ እንዳገር _ እንዳገሯ
ትዘምረው ትደክረው ባድባሯ
ላንተ ምንህ ነው ፍጥርጥሯ?

ሳርፐስቦርግ _ ሕዳር 1992

http://ethioliberty.wordpress.com/

ወደ ምንሳን ጉዞ

መሄድ ነዱ መሄድ_
እየተከደነው
ምድር እየዋጠን
ሠርገን እየዘለቅን
እታች ተዘቅዝቀን
ወደ አዘቅቱ ወርደን
መሄድ ነዱ መሄድ_
ምድር ተከድኖብን
በከርሱ ተውጠን
ከትንፋሽ ተሰብረን...

ሄድነው _ ለጉድ ሄድነው
ተራራ ሰርጉደን
ሸንተረር ሸቅበን
ምድር እየዋጠን
ጨለማ እየጠራን
ብርሃን እየራቀን
ብዙ ጋሻ ገፋን
ብዙ ቀላድ ቆጠርን
በለምለም በረሃ
በተፈጥሮ ሽታ_
ለልም አለ... በሚሉት
ሳጥን ታሽገን
ምድር ሰርጓጅ ሁነን
ሄድነው ተጎንብሰን
ምንሳንን ናፍቀን...

ሄድነው _ ለጉድ ሄድነው
ተፈጥሮን ተጠበን
ከርሱን አስጨንቀን ፥ መሬት ተደፍቶብን

ከድቅድቅ ተዋደን
ጨለማውን ዒጠን
ሄድነው _ ተፈትልከን
እንደ ሾተል ሾልከን...

ሄድነው _ ምድር ለምድር
ተደመን ዘለቅነው
ጥበብ የገራውን
ሰው ያሰገረውን
እያየን ተንዘነው_
መሬት ተደፍቶብን
ጨለማን ዋኘነው
በታሪክ እንድ ቀን
ቀንን አሸነፍነው
አለት ከላይ ሁኖ_
በውስጡ ሾለክነው፤
ከምድር እምብርት አናት
ጨለማን አየነው
በልብ እግር ጉዞ
ምንሳንን ናፈቅነው፤

ኮርያ _ ሰኔ 1981

http://ethioliberty.wordpress.com/

መንገድ ጠያቂ

ስማኝ አንተ መንገድ፣ አቅጣጫህ ወዴት ነው
ልምጣብህ ይሆን ወይ፣ ታዘልቀኝ እንደሆን?
ምጣብኝ ምጣብኝ፣ አይዞህ አታመንታ
ቀና ነው ፈለጌ፣ ሰተቴ ቀጥታ
በምንህ ልመንህ፣ አፋፍ ልታወጣኝ
የመንገድ ምስጢሩ፣ ዘላለም አይገባኝ?
ሰንሻርህ ሳስረዳህ፣ መንገድን ለየቅል
ምንው መንገድ ሁሉ፣ አንድ ነው እምትል?
እዬ ወዳጄ ሆይ፣ መጠርጠርስ ደጉ
መንገድ ሂዶ ሂዶ፣ ከማነው እሚጠጉ?
ተከተለኝ አልኩህ፣ እመነኝ ወዳጄ
ምን ይጠቅመኝ ብለህ፣ አሁን አንተን ክጀ?
ይሁና እንግዲህ፣ መንገድ እንተን ብዬ
ልምጣ ምራኝ ከፊት፣ ይቃና ጉዞዬ
መንገድ ቢሉ መንገድ፣ አይደለሁ መልጋኖ
የያዝኩትን ከያዝኩ፣ ቀን አይቼ አልከና
እንዲያማ ነው እንጂ፣ ከሆኑ መንገድ
በመንትያ እሚጠልፍ፣ መች ሆነ ዘመድ?
መልካም ዘይደሃል፣ እኔን መሻትህ
እሾህ ቆንጥር የለ፣ እግር አንቃሪህ
ከእግርም እግር፣ ግራ ግራውን
መጠንቀቅ አይከፋም፣ እሚያጠቃውን፤

ለብርሃኑ ሃመልማል
አዲሳባ _ መስከረም 1971

ያድዋ ትዝታ

የነጮ እግር፣ በአፍሪካ ምድር ሲተክል
የጥቁር ሕዝብ እርኑት፣ ሲታጎል
እናት አፍሪካን፣ ነጮ ጥምባንሳ ሲናጠቃት
የቅርጭምጭሽ ሲቧጨቃት _ ሲያተራምሳት
ያኔ ነበር... የብራ መብረቅ የጣለው
ነጫጭባውን ዘንጥሎ _ የጥቁርን አምድ የተከለው!

አድዋ ፣ አንቺ የጥቁር ሕዝብ እምቢታ ቀንዲል
ያባቶቻችን ወኔ _ አልበገር ባይ ምስል
እንደምን ነበር ውሎሽ?
እንደምን ነበር ገድልሽ?
የሰዉን አልጠይቅሽ
እሱን... እሱን_
አባ ዳኘው ያውሳልሽ...

ይልቅስ ልጠይቅሽ፣ የነሳቢሳን ውሎ
የነጆቢራን አንዱን ገንጥሎ፣ አንዱን ዘልዝሎ
ምድር ቁና ስትሆን፣ ጎራዴ ጎራዴን ሲላጭ
ጠር በጠር ላይ ሲቀበቀብ፣ እስበሱ ሲናጭ
አሞራ በሰማይ፣ ሲያይሽ ውሎ
ግዳይሽን ሊያነሳ ምሎ...

ደመቅሽ አሉ፣ አድዋ
የጥቁር ሰማይ ሲሳይዋ_
በድል መረዋሽ እልልታ
የጠላት ቅስም ሲረታ_
ያ የለኮስሽው ደመራ
የምንዱባንን ልብ አበራ_
ዝናሽ ለዝንታለም ሲዘክር
የሠሩሽ አላዩ _ ተጭኗቸው አፈር!
(አዲሳባ _ የካቲት 1972)

http://ethioliberty.wordpress.com/

ያልቀናው ዚቀኛ

በቀተረው ተሲዓት _ በሄራው ዝያ
ሲሰብክ አገኘሁት _ ያንን ሃሞርሾ
ሸክም የት አባቱ _ ትክሻ ሰባሪ
እሱ ከላይ ሁኖ _ የሰው ሰው ቀባሪ
አውርዱና ጣሉት _ ይንኮትኮት ይሰበር
ቢሻው ይጨራመት _ ለጉድባ ይቀርቀር
እራሱን ካልቻለ _ ይወርወር ይሸቀንጠር
ኧረ የት አባቱ!... ሸክም ብሎ ነገር...
እያለ ሲያታክት _ መራጅ ወጪውን
ማንም ሰው አልሰማው _ መጥኔ እሱን መሆን!

አሁንም ቀረበ _ ወኖንዲት ወይዘሮ
ዱታ ነኝ እያለ _ ሀጥሩን አንጨፍሮ!
ሴትዮ... ሴትዮ!... እንዳትመጪ አላልኩም
ባይኔም እንዳላይሽ _ ሰው አላኩብሽም?
እና... ትዛዜን ጥሰሽ
ቀኑን አሳሰተሽ_
መምጣትሽ ለምንው _ ዛሬም እንደገና
ተይ አትመላለሽ _ በቫርቫር ጎኖና
በይ ምንደል በይልኝ _ ዳሌሽን ልይበት
ከሱ ጠብ የለኝም _ ካወቅሽ አወቂበት
አለና እንደመብረቅ _ ድንገት ቢጮህባት
ትገባው አጣችው _ ወይም ታመልጥበት!

እሱ ግን አላየም _ ልይልሽ ያላትን
ፊቱን አዞረና _ ጮኸባት ድመትን!
አንቺ ደሞ _ እምቢ አልሽኝ አይደል
ዝሆ እየወጣሽ _ ይህን መሞናደል?
ለምን? ለምን እኮ ነው መሸቀርቀሩ
እኔን ለመምሰል መጣሩ?
ደሞ ከረባቴን እያሰርሽ

ነጭ ልብሴን እየለበስሽ
ጫማዬን ተጫምተሽ
ሰዓቴን አድርገሽ
በደራ ዝለያ በሞላው መስላታ
ልታስነጥቂኝ ነው _ በዚህ በቱማታ?
በይ አምጪ አውልቂ... መልሺ ልብሶቼን
ቁሚ፡ ቁሚ ብዬሻለሁ!... ወይ አንቺን ማመን...
አለና ድመትዋን _ ማባረር ጀመረ
ድንጋይ ቢወረውር _ መስታወት ሰበረ።

ያውቶሞቢል ጌታ _ ከጋቢናው ወጣ
ያንን ሃዋርያ _ በሕጉ ሊያስቀጣ፤
ምንው? ምንው የኔ ወንድም
መኪናና ድመት _ ለይተህ አታውቅም?
ና በል በሕግ አምላክ _ የትም አታመልጥም
ወደ ሕግ እንሂድ _ ወደድክም ጠላህም!...
አለና ጠርንቁ _ ጉሮሮውን ያዘው
ሃዋርያው ሲስቅ _ እሱ እየበገነው፤
እኔና አንተ? እኔና አንተ አንታረቅም
አልፈልግም... አልፈልግም ወንድም
ሰማ ... ደብዳቤዬን ወዴት አደረስከው
ለማዬ ሰጠሃት ወይስ ቀደህ ጣልከው?
ብቻ ተወው... ተወው አታንበው
ሌላ _ ሌላ አዲስ እጽፋለሁ
ብቻ _ ብቻ ላባባ አታሳየው
አንተው _ አንተው ለብቻህ ጥዝው
ጥዝው ኮምክመው _ አንጀትክን አርሰው
ብቻ _ ብቻ አታልቅስ
አምባ አታላይ ነው ሰው አሚያልፈሰፍስ
አቤት... እንዴት አምሮብሃል
እንደኔው ደልቶሃል
አፕ_ አፕላስ ፓፓፓ... በጣም ትክብዳለህ
ላንሳህ አልቻልኩም _ ብዙ ትበላለህ
ሰውዬው አፍጠ _ ድርሳኑን ሲሰማ

http://ethioliberty.wordpress.com/

ሕዝቡ ከቦ ቆመ _ ድርጊቱን ሊሻማ፤

እንቅ ወንድመ ነው መሰል
ያም ደንግጠ ቆሟል
ያም ያጫወተዋል
.....
እንዲያው ባሞር ቀረ
እንዴት የተማረ የተመራመረ
ምሁር መሰላችሁ _ ኮሌጅ የነበረ
.....
አዩ የለየለት _ ጨርቁን የቀደደ
ቢያጠፋ አይጠየቅ _ ሰው አንዴ ላበደ
.....
እንቅ ተፋጠዋል
ይቅር ለእግዚር እንደሁ _
ምስጢሩን ማን ያውቃል?
.....
ይላል ያ ሁሉ ሰው _ የመሰለውን
ገላጋይም የለ _ የዳኛ ሀቡን፤

ሰውዬው ሲበቃው _ ሲሚጠጥ ትግስቱ
በቡጢ ነደለው _ አልችል ቢለው ውስጡ፤
ማንም አልጠየቀው _ ሃዋርያው ቄሮር
እመኪናው ገብቶ _ ቁልቁለቱን ሲበር፤

ወዲያው ሃዋርያው _ ትምርቱን ቀጠለ
ሕልም ይፈታ ጀመር _ ሕዝብ እያስተማረ፤
ዝናመ ማታ ቢቴ መጥቶ
ልብሴን አበሸቅጠ አበሸቅጠ
እንግዲህ ልብ በሉ
መሸሚ ነው አሉ...
ቦሚዬ ሰልክ ደውላ
አበል ቡና ስታፈላ
እንግዲህ ልብ በሉ

ቀበሌ ጠራኝ አሉ...
ጨለማው ከሰው ጋር ተጣልቶ
ያገኘውን ሁሉ ፈንክቶ ፈንክቶ
እንግዲህ ልብ በሉ
መሞቴ ነው አሉ...
አባቴ ቢተክስያን ሂዶ
ቅዳሴ አስቀደሶ
እንግዲህ ልብ በሉ
ገንዘቤን አልመልስ አሉ...
ቤቴ በጦብ ተሠርቶ
አልጋዬ ተንጥፎ
እንግዲህ ልብ በሉ
ሽክም ቀረ አሉ...
ቴሌቪዥን ቤቴ መጥቶ
ሲለድበኝ አምሽቶ
እንግዲህ ልብ በሉ
ሥራ ገባሁ አሉ...
አንድ ሰውዬ ተሰቅሎ
ቀኑን መሉ ተንጠልጥሎ
እንግዲህ ልብ በሉ
ላገባ ነው አሉ...
አለና ሃዋርያው _ በድንገት ዘፍ አለ
ከቦት የቆየው ሰው _ ወዲያው ተገለለ፤
ማንም አልተጠጋው _ ምን ሆንክ ያለው የለም
ጥርሱ ፈገግ አለ _ ከከንፈሩ ሽርመም፤
ማንም አላቀናው _ እሱም አልጠበቀው
ስብከቱን ሳይጨርስ _ የበላይ አስጠራው፤

አዲሳባ _ ጥቅምት 1977

http://ethioliberty.wordpress.com/

ጨዋ... ከመቦል ጅርባ

ዐይን ያለው ያላየብህ_
ጆሮ ያለው ያልሰማብህ
አፍ ያለው ያልጮኸብህ_
እጅ ያለው ያልጻፈብህ
አንተ ማነህ?
ማነህ ያጤው ዘመን ሹመኛ
የብዙሃኑ እግረ መውቅ፤ የኔ ብጤው ደመኛ?
ማይምነት...
ያንተም አበቅቴ ቀረበ
ወገን ሀሡ ... እያለ ተጠበበ
የስብስቴው ምሽግህ ፈረሰብህ
አሃዱ ክልሌቱ... እያለ አሰላብህ
ከእንግዲህ ምን ይዋጥህ
ተሠርቶ መፍረስ አልቀረልህ
ጨዋ... መባል ቀረብህ
ወየው ላንተ... ወዮልህ...

አዲሳባ _ ጥቅምት 1972

ዝክረ ናይሮቢ

እጀብ እንጂ_ ናይሮቢ
የጅኒው ብዛት አንደርቢ_
በማታቱው ተምታቶ
በአረያው አቅል አጥቶ
እጀብ እንጂ_ ናይሮቢ
ነፍስ ውጪ ነፍስ ግቢ...

ጠቢያ ሰልቶ
ዋቴው ዋቶ
ባሥር አንድ ገዝቶ
ካንዱ ነጥቶ_ ሳንዱ ሰጥቶ_
ናይሮቢን አስለቅሶ፣ አስጨንብሶ
ኩኩዩውን፣ ባንያኑን፣ መሳዩን አስጎንብሶ
አሱም በተራው_
ላስካራው እርቦ አፍስሶ
ለቡሊሱ፣ ለሲአይዲው አጎንብሶ፤
እጀብ እንጂ_ ናይሮቢ
መተት አይሉት አንደርቢ...

ጀለው ለግላጋው፣ ዋርዳ ሳመና መሳዩ
ኩኩዩው፣ ካለንጂኑ_ ለምን ኒኢኪ (መጢ) አየሁ ባዩ
ሃንግ ይለዋል፣ በየጥሻው በየጉድባው
ንዋይ ፍለጋ፣ የሚዋትተው ወጠምሻው
እነ ሃበሽ፣ እነ ኦርያ ዐይጢትን ሁነው
ድመት ባንቱን ሲኮንኑ፣ በላጌ ሰብ ነው ብለው
እጀብ እንጂ_ ናይሮቢ
ያገር የለሽ ሳማ ዶቢ...

አንቺ ኪንያ ... እህት ምድር
አንቺ ናይሮቢ ... እፌትና ማር
ምነው ጨክትሽ በረከተ፣ ሃጥእሽ ደጅሽ ሞላ

የእግዜሩ መንገድ ተረስቶ፣ ሸፍጥ ዘረፋ ፈላ?
አደይ ጽጌሽ ረግፎ፣ እሾህ አሜኬላሽ አጎንቁሎ
ማን ይወዳጅ ከኩኩዩ፣ ማን ይጠጋ ከጀሉ?
ማን ይብላ ከኡጋሊሽ፣ ማን ይጠጣ ከወተትሽ
እንግዳ መያዝ፣ ከቶም ከቶም አልሆነልሽ፤
እጀብ እንጂ_ ናይሮቢ
የጅኒሽ ብዛት አንደርቢ...

የሰው ልጅ ልቡናው ተሰውሮ
ባዘን በጭንቀት ነፍሮ
አንዴ በጫቱ መርቅኖ
አንዴ በባንጊው ታጥኖ
አንዴም በቺፑጊ ተጉኖ
አንዴም በቻንጋ፣ በቻም ቻም በኖ
ጠቢያ ሳይቀር፣ ባንቺ አዚም ሰይጥኖ
በዚያ ላይ_ ፖሊ ፖሊን ተክኖ
ምኑ ቅጥሽ ናሮቢ፣ እጀብ እንጂ ነሽ አንቺ
በበር መለስ ግብግሽ፣ ባኮርባጅ ጡጫ ስትረቺ፤
እጀብ እንጂ ናይሮቢ
ሚርት አይሉት አንደርቢ...

ጠቢያም ዋዛ አልሆነ፣ ያስካሪን ቁቁ ሉጃ!... እየጠጣ
በየወህኒው እየታሸ፣ ለሱና ቤሳም ቢቀጣ
እፍኝ መሉ ሽልንግ እየዘገነ
ውስጥ አንጀቱ እየደበነ
ሃባሪያኮ_ እንደምነሀ? ሲሉት
ደሀና ነኝ ይለዋል_ መሙሪ ሳናን ለምዶት፤
እጀብ እንጂ ናይሮቢ
ነፍስ ውጪ ነፍስ ግቢ...

ለሱና ሺፋ_ ችግር የለም ሁኖ_
ሕይወት ጥብጥቢ
የሰው ልጅ ይታሻል_ በመከራ ሳማ በመከራ ዶቢ፤
አወይ ጠቢያ... አወይ ሶማል

http://ethioliberty.wordpress.com/

መገልመጡን መገፋቱን ያስታምማል
እስክስክስክስ... ይሉት ጥቅሻ ማዳመጡ
እንደ ፍየል መጎተቱ፣ መቀጥቀጡ
ከዋልዳ ቲካ፣ ከቲካ ይፎ መጎተቱ
ካኩማ ኬዝ፣ ማራፋ ኬዝ መሰኘቱ
በእስሊ በረት መታጎሩ
ካሩባንጌን መወጠሩ
ቢባ ቢሻን መዘመሩ
ሳሬ ሳሬን መገበሩ
አጀብ እንጂ ናይሮቢ
የምድር ሲኦል አንደርቢ...

አገር የለሽ መጻተኛ
ማረፊያ የለው መኖ፣
ኡጋሊ የለው ማቶሪ
ጌይሬ የለው ቻፓቲ
ሱኩማ የለው ማንዳዚ
አንጀቱ ታጥፎ ሁሰዜ፣
ማላ በመላ እየበላ
ቁርስ በብርድ ልብስ እየከላ
ምሳ በዝግኒ እየቀላ
መክሰስ ዶቮቬሌን እያሰላ
እራት ቪኦኤን እየሞላ
ሱጂሞን እያብላላ
እንዲህ ይኖራል _ በመላ...
አወይ ኬኖ አወይ ኢስሊ
መቶ ታምሳ ስቅየቱ_
ምጃም አይደል ወይ እምቢሊ
አጀብ እንጂ ናይሮቢ
የምድር ሲኦል አንደርቢ...

በኬንያ ለሚኖሩ ኢትዮ/ሶማሊ የፖለቲካ ስደተኞች
አስትሊ _ ታኅሣሥ 1991

http://ethioliberty.wordpress.com/

መሞት

ጥበብ ነው _ እንደሌሎች ሁሉ
የማይታበል ገባሬ ቃሉ_
እናም እከይነው _ እጠበበው አሳምሬ
እፈቅደዋለሁና ... እናንተን ሰላይደለሁ_
እናም እሠራዋለሁ
እሠራዋለሁ ወዳጆቼ_
የሲኦሉን መንትያ
የሰማይ ቤቱን በረኛ
እከይነው _
እጠበበው አሳምሬ
ጥበብ ነውና_
ተሱ ራሱ ግጥሚ!

በሲልቪያ ፕላት
ትርጉም፣ አዲሳባ _ የካቲት 1988

ሰማይና ጣና

ኩልል ያለ ሰማይ_
ምድርን ተንተርሶ
ልብን ያማልላል
ዐይነ ርግብን ጥሶ፤
ሲያዩት ጥጋት የለው
እድማስ አይጋርደው
መሄድን ነው እሱ_
ልማድ ያደረገው፤

ሰማይ ምድር ሁኖ_
ምድር ሰማይ ታኮ
እንደ ወለላ ማር
ዐይናችን ስር ጠሎ፤
በላነው ጠጣነው
ኮመኮምነው እንጅ_
ጣና ያባይን ግት
የግዮኔን ልጅ፤

ባሕር ዳር _ መጋቢት 1989

እማኝ ልብሴ

መስክሪ ምድራቱ
አብረን የኖርኒቱ
ምንም ሳልናገር
ትንፋሽ ሳልቋጠር
እንዴት ሰማኝ ጠፈር
እንዴት እማኝ አገር?

ሀረር _ ሚያዝያ 1989

http://ethioliberty.wordpress.com/

ያ የኛ አበበ

እውን አንቺ የሮም አሞራ
ሌላ እግር ሁኖ በረራ
የሚመች ነው _ የሚደላ
ጠጠር ውስጥ እግርን እየበላ?...

አገር ላገር _ ቆላ ደጋ
መብረር... እኔነትን ፍለጋ
እውን ይቻላል _ አንቺ አሞራ
ውድድር _ ካንቺ ጋራ
ሽቅብ ቁልቁል በረራ
የኔ ብጤ ቢጠራ?

አዲሳባ _ ጥር 1965

http://ethioliberty.wordpress.com/

የተውነው ቤታችን

ያዳራሹ ስፋት_
የእልፍኙ ክፍክፋት
የጥራሩ ወሰል
የሳጠራው ሌማት
የጣሪያው ሰንበሌጥ
የማብሰያው ማጀት
የክብቶቹ በረት
የጎታው ሰልፈኛ
ያራሹ መተኛ
የቆጡ አሠራር
የባጡ አደራር
የመደቡ ጽዳት
ያጎዛው ንጥፋት
እድሜ ጠገቡ አጥር
የአጸዱ ልዩ ሕብር
እሾሁ ቆንጥሩ_
ቀጨሞው በቅሎበት
እድሜውን ያወጋል_
ሽበት ተኝቶበት
እኛን አሳልፎ
ሌላ እኛን ሊያይበት?
ከትዝታ ኩሬ
ሰው እያጠለቀ
አገር ቤት አየለ
ቀልብ እያመጠቀ?

ለክተማ፥ ለተረፈ፥ ለግዛው፥ ለግርማ፥
ለተሾመና ለአብሮ አደጎቻችን
ወሊሶ _ መስከረም 1965

ባለቅኔዎች

ሙዚቃ ቀማሪዎቿ _ እኛ ነን
እኛ የሕልሞች ሁሉ _ አላሚዎች ነን
የባህር ሁዳድ በላቾችን _ የምናደንቅ
በተመስጦ ተቀምጠን _ ተመስጠን ራሱን የምንጨንቅ፤

ዓለም ጤዘኖችና ዓለም ብራዎች
በጠፍ ጨረቃ ሲደምቁ_
እኛ ነን ... የሸማኔው መቂናጥ
እንደ ማእበል _ ስናናውጥ
እንደ ጎመራ _ ስናናንጥ
ዓለም ሠናይን _ የምናቂት
እኛ ነን ... እስተወዲያኛው የምናምጥ፤

በኢ. አሻግሬ
ትርጉም፤ አዲሳባ _ ሰኔ 1982

http://ethioliberty.wordpress.com/

የመቀነት ጣጣ

እጅግ የምወድህ፣ አንቱ ቱሌራ
ብርቱ ምስጢር አለኝ፣ ሳንተ የሚወራ፤
እውን በኛ መንደር፣ በዚች በቀበሌ
የምወደውን ልጅ፣ መረጠኝ መባሌ፤
ያስከፋኝ ይሆን ወይ፣ ቆሞ ከመቅረት?
የሰው አፍ አስፈራኝ፣ መላ ምታበት፤

እውነትም እንግና፣ ባእድ ዘና አመጣሽ
ዝርዝሩን ልስማና፣ መፍትሄ ብሻልሽ፤
መቼም ከኔ ሌላ፣ ለንቺስ ማን አለሽ
ልጅ ሆዴ ሙሉ፣ ምን ይሆን ሃሳብሽ?

መቼም ታውቀዋለህ፣ ወንድም እህት አለኝ
ካራት ሴቶች መሃል፣ ታላቋም እኔ ነኝ፤
ባገራችን ባህል፣ በወጉ በደምቡ
ታላቆች እያሉ፣ ከታናናሾቹ መቼም እያዝቡ፤
ስለዚህ ጋሽዬ፣ እድሜዬ እየገፋ ጡቴ እየወደቀ
እኔን የሚያገባ፣ አንድ አስካልጠየቀ
እስከ መቼ ልቆይ፣ ነፍሴ ተጨነቀ?

ለሱስ እውነትሽን ነው፣ ሰንቶቹ ተዳሩ
ሦስት ጉልቻ ሠርተው፣ ሀብት ልጅ አፈሩ፤
ለንቺ ማን አድሉ፣ ለልደርስሽ እያለ
ባንቺ የተነሳ፣ ሴቱ ከቤት ዋለ፤
ስለዚህ ማና አሱ፣ ወይንሽ ያረብት
ንገሪኝ መልዬ፣ መላ እንድልበት፤

ልጁ እንኳን እውቅ ነው፣ በመንደራችን
ቤተሰቡም ጨዋ ፣ ነባር ባምባችን፤
ሜልቺሳ ይባላል፣ ያቶ ፈይሳ ልጅ
መልክ መልካም ሽጋ፣ ጨዋታ ጨዳጅ፤

http://ethioliberty.wordpress.com/

ፀባዩም ወርቅ ነው፣ ከጉብሎቸ ሁሉ
ግብርናን ይወዳል፣ ይኸው ነው አመሉ፤

እንዲያው ባጋጣማ፣ ሲያልፍ ሲያገድም
ለሱ ያለሽን ፍቅር፣ እንዲያውቀው አሱም
ሞክረሽ ነበር ወይ፣ በብርቱ ሰላምታ
ልቡ እንዲገብር፣ ስሜቱ እንዲረታ?

የለም አልሞክርኩም፣ መች እድል አግኝቼ
ፈጭቼ ሳቦካ፣ መች ከቤት ወጥቼ፤
ጠዋት ማታ በሥራ፣ ከቤት ተወስኜ
ከንፈር ወዳጅ አላውቅ፣ ከጓዳ ታፍኜ፤
ለዚያውም ሃሜቱ፣ አልቀረልኝ ጋሼ
እንደ ስንክል በቅሎ፣ ሁለዜ አጎንብሼ፤

ምንድነው ሃሜቱ፣ ምንድን ሆነ አሉ
ሰው ከሰው ራስ አይወርድ፣ ክፉ ነው አመሉ?

ሕግ የላትም ብለው፣ አናገባት አሉ
መልክ የላትም ብለው፣ አናፈቅራት አሉ፤
ገልቱ ናት ተብላ፣ ተንቃፈች አሉ
የድሃ ልጅ ብለው፣ አንቀርባትም አሉ፤
እያሉ ሲያኝኩኝ፣ ጅሮዬ እየሰማ
ጋሼ መኖር ጠላሁ፣ ከእንዲህ ያለው ዝማ፤
ደሞም የህቶቼን፣ እድል ሰባብሬ
የምኖር መሆኔን፣ ሰማሁ በመንደሬ፤
ስለዚህ ጋሽዬ፣ ሞንቂን ተረድተህ
መላ ፈልግልኝ፣ በቱም ሞትኩልህ፤

ያም ይበል ያም ይበል፣ የመሰለውን
አንቺ ግን መሉ ነሽ፣ አርቪው ሃሜቱን፤
ይልቅስ ልንዝርሽ፣ የሚሆነውን...
ሜልቺሳን መሞለፍ ነው፣ የወደድሽውን፤
ልንዝርሽ የኔ ልጅ፣ የሰው ልጅ ግብዝ ነው

እሱ የተመኘውን፣ ማግኘቱ ሲያቅተው
እድሉ ነው ይላል፣ ያልሞከረውን
ሌላው ሲሞክረው፣ የጨበጠውን...
እግዚኦ... እግዚኦ... ይላል፣ ነገሩን አዳንቆ
ዘውሰጣዊ ቅናት፣ ተንገብግቦ ዘሸቆ፤
ምናልባት ላንዳፍታ፣ መስታወት ዘርግቶ
ልቡን ዘልቆ ቢያየው፣ መሰሎቶቹን ከፍቶ
ስንት ጎጢዓትና፣ ስንት ወንጀል ሠርቶ፤
ስንት በደል ፈጽሞ፣ ስንት ግፍ ፈጽሞ
ተሸፋፍኖ አንዳለ፣ ተውጠ ባርምሞ፤
ባወቀው ነበረ፣ ራስ ውስጥን ፈትሾ
ሌላን ከመኮነን፣ ከማውረድም ሙሾ፤
ስለዚህ መልዬ፣ ያበጠው ይፈንዳ
ለሃሜት ይሉኝታው፣ እንዳትሰጪ ፋይዳ፤
ያሰብሽውን ሁሉ፣ ፈጽሚ ጠንክረሽ
ለጠለፋው ጉዳይ፣ ይርዱሽ ወንድሞችሽ፤
ደሞም ልብ በይ፣ ሳይሆን የሚሆነው
ጉድና ድንቅ እኮ፣ ወዳንድ ሰሞን ነው፤

እሺ ጋሼ ሆዴ፣ ምክርህ ውስጤ ገብቷል
እንዳልከኝ ለማድረግ፣ ልቤ ተነሳስቷል፤
አለችና ልጂት፣ እጅ ነስታ ወጥታ
ሁሉንም መከረች፣ ወንድሞቿን ጠርታ፤

ሦስቱ ጎበዛዞች፣ ወንድሞቿም አሉ
ሕልምሽ እውን ሆኖ፣ እንዲታየን ውሉ፤
ከጎንሽ ቆመናል፣ እታለም መልዬ
አሀት ወንድሞችሽ፣ ለባባና እማዬ፤
ቆማ ቀር ተብለሽ፣ ታምተሽ ተቦቷቀሽ
እስከመቼ ድረስ፣ ቆስለሽ ተንገብግበሽ?
አንቺ አፍንጫ ሆነሽ፣ ሁሉ ሰትመቺ
እኛም አይን ነበርን፣ ሰናለቅስ ላንቺ፤
አሉና በስሜት፣ ፎከረው ዝተው
ሜልቺሳን ፍለጋ፣ ወጡ እንደ ሁነው፤

ማማሸ ቀን አድነው፡ የማታ የማታ
ጫልቺሳን አገኙት፡ ካንዲት ከተብታ፤
እንዳነራው ባህል፡ እንዳ እንደጥንቱ
ጠለፋ ሲከወን፡ ወግና ሥርዓቱ
እርጥብ ሳር ተነጭቶ፡ ካሹት ላይ መጣሉ፤
ያለ የነበር ናሮ፡ ሙሉም አልዘነጋች
እርጥብ ሳር ነጫጭታ፡ ጫልቺሳ ላይ ጣለች ፤
ይኸኔ ወንድሞቿ፡ ተጠመጠመቡበት
የወሳንሳ ይዘው፡ ሜሪሎ... አሰቡት፤
ጠለፋ መሆኑ፡ ጉዳዩ ሲገባው
ጫልቺሳ ዞረበት፡ መፎህ እንኳን ጠፋው፤
ፈርገጥገጥ ሲልም፡ እጅ እግሩ ታፈፈ
ሃይሎጋው አይሎ፡ ባየር ላይ ሰፈፈ፤

የግራር ጃርሶዋ ፡ ቱለኒ መንደር
ዜናውን ሞቀችው፡ ከዳር እስከዳር፤
ካንት ቶሌራ ቤት፡ የወጉ ደረሰ
ተበላ ተጠጣ፡ ጫጉላው ተጫጫሰ፤
አዎን ጉድና ድንቅ፡ ላንደዜ አለፈ
ሙሉም ወግ ደረሳት፡ ትዳር ተጨለፈ፤
እነዚያ እህቶቿም፡ ከእስር ተለቀቁ
ሦስት ጉልቻ ሠርተው፡ መንደሩን ለቀቁ፤

+ የእውነተኛው ድርጊት ዜና ምንጭ
ለሆኑት ለአባባ በቀለ ደማፈ
አራተ ማርያም፡ ሰላሌ _ ጥር 1975

http://ethioliberty.wordpress.com/

ጋዜጠኛው

እንጀራህን ያላወቀ
ግና ስንቱ ፡ ያግቦ ፀጉር ሰነጠቀ
መጥኔ ላንተስ ... ደፋ ቀና
ሹም እናግረህ _ ምንዝር መና
ምንዝር ጠርተህ _ ሹም ልመና
መጥኔ ላንተስ ... ለእስትንፋስህ
ኖርክ አልኖርክ _ ማን አውቆልህ?

መጥኔ ላንተስ፡ መጥኔ ለጣህ
ውቃቢ ርቆህ፡ ወዳጅ ነጥፎህ
የነከስካትን ለማትለቅ
ያንተይቱ ጣይ፡ ለማጠልቅ
የራስክን ሃቅ፡ ለማትሰርቅ
መጥኔ ላንተስ፡ ለብቸኛው
የቁርጡ ቀን፡ ጠረኛው፤

መጥኔ ላንተስ፡ አባ ግዴ
ጠላው ቀጭን፡ ሃታው ጓዴ
መጥኔ ላንተስ፡ ላዚመኛው
ላገር ውጋት፡ ዋግምተኛው
ቅጠል ሳበጥስ፡ ስር ሳትምስ
ሳትቀጠቅጥ_
ሳትጨቀጭቅ_
ሰራዬ አገር፡ ለቀመምከው
መጥኔ ላንተስ... ጋዜጠኛው፤

አዲሳባ _ መጋቢት 1973

ያልታደለች እልፍኝ

ማን ኑሯል የተኛው እዚህ
መኔ መምጣት አስቀድሞ
ማንስ ኖረባት ይቺን እልፍኝ
እንዴትስ ተስተውሎ
እውን...
ዱባና ቅል
ወይስ...
የነበረ ተማስሎ?
ኮረዲት እንድያዋን ኑራ
ወይስ ተባልንጀር_
ከክበሌው ጋራ?

እልፍኟ መሊት አጢሟት
ያውም...
የምቦቀቂላ መስህብ ሽንት
ያውም...
የሃሌት ፍልቅልቅ ውበት
ያውም...
የቸበርቻቻ ሕልሞች መሊት_
ያለያም የብቻ ብቸኝነትን የመረጠ
ባዶ አልጋን የታቀፈ
ወና ጓዳ ጎድጓዳን ያጨመተ
ምኑን (መናኝ) ቀበሌ ይሆን?
ያለያም የብቻ ብቸኝነቱን የመረጠ
ሁሌም የሃዘን ድባብ ያጠላበት
ያልታደለ የሃቻምናምና ጎጆ ይሆን?
እናም...
ምኑን አምባ፣ ምኑን ቀበሌ እንበለው ይሆን?
እናም የእልፍኙ ተጠቅሮ እድሜ ሲለካ_
ምን ያህል ዘመን፣ ያስቆጥር ይሆን?

http://ethioliberty.wordpress.com/

እያቀነቀነች_
እያንጎራጎረች_
እየዘፋፈነች...
ዳንኪራውን ረግማ_
እስክስታ እየመታች
ትኖር የነበረች
አንዲት ውብ ኮረዳ
ተይህ ግድም ኑራን?
ያስ የምሳ ይቅረብ ደወሉ
የድረሱልኝ ጥሪ ነጋሪው
እንደ ብሔቱ፣ እንደብሔቱ
ተዚህም እልፍኝ ኑሯል?
እናም...
እንደኔ እንዳሁኑ ሁነቱ
ተይህ ቀደም...
ተዚህ ተቆምኩበት ወሰል
አንዳች የሰው ዘር ቁሞ ኑሯል?
እኔ እንጃ!...

እውን ያን ሰው
ስመ-ን አውቂው
መልኩን ለይቼው ይሆን?
እናም እውን...
ያው የጥንቱ ውብ ስፍራ ሁኖ
አንዱ ፈንድቆበት_
አንዱ ደሞ አልቅሶበት ይሆን?
ታማኙ ውሻ ችሎ ማደር_
ኩንስንሷ ውርዬ ብጥርቅኑ
ደንገላሳ የሚፈሰው ቦራው ፈረስ
ያለያም ቤተኛይቱ የጓዳዋ ዐይጥ
ተዚህ እልፍኝ፣ ተዚህ ስፍራ ኑረዋል?
እኮ ማን ነበር_
ማን ነበር ተዚህ?
እኮ ማንስ ያውቀዋል፣ ይህን እልፍኝ

ተኔስ እውቂያ ይኖረን ይሆን
በውል ያውቁኝ ይሆን አነሱ? ወይንስ እኔ?
ይገርማል!...

ማት ለብሰው፣ አጋርደው፣ አሸርጠው
መኾ እያወረዱ፣ ደረት እየደቁ_
እዚህ ግድም ሳሉ የኔ ብጤዎች
ሩሄ ያውቀዋል፣ ቀልቤ ይረዳዋል።
እምባቸው እንደጎርፍ ሲወርድ
ወለል ብሎ ይታየኛል
ይገርማል!...

እናም ታንጀቴ እወዳቸዋለሁ
አፈቅራቸዋለሁ...
እልፍኙ አዲስ ነው_
ቤት ለእምቦሳ የሚባልለት
በእጅ መንሻ የሚካድመት
የባለቤቶቹ አንጡራ ሃብት
ማንም ማንም የማያዝበት
አንዳች ለውጥ የሌለበት
ዛሬም እንደጥንቱ ያለ
የነበረና...
ወደፊትም የሚኖር?

እናም በአልፋ ኦሜጋ አበቅቴ
እስተ ማእዜኑ የሚኖር
እናማ አሁን...
አሁንማ እልፍኙ
የግሌ ጉልት
የራሴ አርስት ነው?

በዳንዔላ አስቴል
ነፃ ትርጉም፣ አዲሳባ _ 1987

http://ethioliberty.wordpress.com/

እስቲ ትንሽ እንመት

ዛሬም እንደ ትናንት
ኢሉሂ ላንዘምር
እግዚኦታን ላንጠራ
ችጋር ሕልመኑን ሸሮ
ቤት አውል ሲሳቡን
ትውልድ እንዲጠራ
እስቲ ትንሽ እንመት
አሻፈረን እንበል...

ችግር እንዳይበልጠን
እኛ እሱን እንብለጥ
ርሃብ እንዳይጠልፈን
እኛ እሱን እንጥለፍ
መታረዝ ላይበርደን
እኛ እሱን እንቅደም?
ታመናል እንበል
መሮናል እንበል
ከብዶናል እንበል
ከጫንቃችን ወርዶ
ሸክማችን ይቅለለን
እስቲ ትንሽ እንመት
አሻፈረን እንበል...

እስቲ ዘንድሮ እንኳን፣ እንዳደይ እንብቀል
ጽጌረዳ ሁነን_
ወዳጅን አድምቀን
ጠላትን እንውጋ
እኛ ለእኛ እንመት፣ ካጋም አንጠጋ?
እኛ ለእኛ እንመት፣ እንሁን ለጠቢያ
አንድ ግዳይ እንጣል፣ ለታሪክ መታያ?

መች ለየግላችን፣ መች ላንድ ራሳችን
አዳኛችን ጎሎ፣ ወሀኒ መጣላችን፤
እስቲ ትንሽ እንመት
አሻፈረን እንበል...

ዛሬም እንደ ትናንት፣ እንሞክር እንጣር
የትናንቱ ባይሰምር፣ ከዛሬው እንጀምር
አኪራችን ቀንቶን፣ ትልማችን ፈር ይዞ
ምናልባት ማን ያውቃል፣ ይሳካል ይህ ጉዞ፤
ዳዴ አይናቅም፣ ሀሁ... አይጠላም
ታልጀመሩ በቀር፣ ተዳር አይወጣም፤
ታመናል እንበል
መሮናል እንበል
ከብዶናል እንበል
ከጫንቃችን ወርዶ
ሸክማችን ይቅለለን
እስቲ ትንሽ እንመት
አሻፈረን እንበል...

ለፕሮፌሰር አሥራት ወ/የስ
ለፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም
ሳርፕስቦርግ_ ግንቦት 1993

http://ethioliberty.wordpress.com/

እኔና ልቤ

እያየሁት እየኖርኩት
እልሄን እየበላሁት
ስንቱን ዘመን
ስንቱን መሆን ሆንኩት፤
እንዴት ትሆን? እንዴት ትሆን ልቤ
ምሬት ውጠህ፣ ችግር ነክሰህ ቀልቤ?

መኖርን እወትበት፣ እባክህ ልቤ ወዳጄ
አንቸጋገር... አንተም ተጨንቀህ፣ እኔም ተሰድጄ፤
ያይኔ ብርሃናት፣ ያጥንቴ ክፉይ ልጆቼ
ከሩቅ ሁነው ሲጠሩኝ፣ ወይ እምልበት አቅም አጥቼ_
ታየኛለህ ልቤ፣ ትታዘባለህ ብጤቴን
አንድዬ እንጂ ምላሽ ሰጪ፣ መች እኔና አንተ ሁነን፤

እናም... ቻለው ወዳጄ ልቤ
ያለሚቱን ረቂቅ ምስጢር_
እኔ አልዘልቅም አስቤ፤
እሱ አለ _ ፍርድ አደላዳዩ ያለም ዳኛ
ልቤ አደብ ግዛ፣ ሁሉን ላንድዬ ትቼ ልተኛ፤

አስትሊ _ ጥር 1991

http://ethioliberty.wordpress.com/

ሊነጋጋ ሲል...

ኡፍ!...
ደሞ ነጋ ፥ ዛሬን ሆነ
ደሞ ጠባ ፥ ትናንት ተከደነ
ደሞ ነጋ ፥ ይኸ ጭጋግ
ደሞ ጠባ ፥ ይኸ ልጋግ
ኡፍ!...
ሊነጋጋ ሲል ጨልሞ
ከድቅድቅ አስጥሞ
ከብርሃን ናፍቆት አፋልሞ
እውን ደሞ ነጋ ፥ ዛሬን ሆነ
ጭለማ ንግር ሁኖ ፥ ነግሁን አፋነ?

እስቲ ይሁን_ ይመስገነው
ደሞ ይነጋ ዛሬን ይሁን
ደሞ ይጥባ ነገን ይሁን
ሊነጋጋ ሲል ጨልሞ
ተስፋ ለራበው ተመጽውቶ
በድቅድቁ አጨቅይቶ
ጽልመት ትንቢት ሁኖ
ሌላ ቀን ሊያጠባ_
ከቻለማ መልካም
ሊነጋጋ ሲል ሲጨልም...

ሳርፕስቦርግ _ ግንቦት 1993

ትውፊታዊ ምልልስ

http://ethioliberty.wordpress.com/

የሴት ነገር

“ ፍቅርዬ አንተም እንደሌላ? ”

“ አልገባኝም_ ምን ለማለት ፈልገሽ ነው? ”

“ ሌቶች ስትባሉ? አልከኝኮ! ”

“ ታዲያ ምን አጠፋሁ? እውነት አይደለም እንዴ? ”

“ ተው እንጂ ፍቅሬ_ አንተም ያባቶችህ ልጅ አትሁንብኝ ”

“ *ወንድ ልጅ ተወልዶ፣ ታልሆነ እንዳባቱ አመልማሉ ስሙት፣ ይፍታል እንደናቱ*” መባሉ ታዲያ ለመቼ ነው? ”

“ ይገርማል ክፉ ክፉው ሁሉ በሴቶች ላይ ሲተረት ተኑሯል”

“ ታዲያ ምን አስጨነቃችሁ፣ ያልሆናችሁትን አያሏችሁ ”

“ አባቴ ይመኑት፣ አሁንስ አንተም ከነሱ ባለክብኝ ”

“ ለመሆኑ ምኑ ነው እንዲህ ያንገበገበሽ? ”

“ እሮጌ ተረቱና ምሳሌው ሁሉ ሴትን የሚያራክስ ነው”

“ ለምሳሌ?....”

“ *ሴት ማገደ ቢቸግራት፣ ምሰሶ ትንቀንቃለች* የሚለው ዓይነት ”

“ የዚህ ዓይነትማ ብዙ ብዙ አለ፣ እስቲ ጨመርመር

አርጊበት ''

'' ምን ሊጠቅመኝ? እናንተው እንደጀመራችሁት መራር ቂበት እንጂ''

'' እኛማ ሴት ከበዛ ፣ ጦመን ጠነዛም እንላለን ''

'' ሌላስ? ''

'' ሴት ለቤት ፣ ወፍጮ ለዱቄት ''

'' ሌላስ? ''

'' ሴት በማጀቱ ፣ ወንድ በችሎቱም ይባላል ''

'' እማዬ ትመኑት አሁንስ አበዛችሁት! ''

'' ኧረ ቆይ ! ሌላም አለ... ሴትና ቂሰ ቀሰ በቀሲ...''

'' ወይ ጉድ ! ...''

'' ሴትና ቤት አይታመንም ''

'' ውሸት ውሸት ! አሁን እኔ አልታመንም? ''

'' ተይ እንጂ አንቺማ ነፍሰ ልጅ ነሽ፣ ይህ ለሌሎቹ የተባለ ነው''

'' አይመስለኝም። ብቻ እሺ ይሁንልህ... አንተ እስካልጠላኸኝ እኔ ምን ቸገረኝ ያሉትን ቢሉ ''

'' እወድሻለሁ የኔ ወለላ... ልቀጥልልሽ? ''

'' አ.ም.ን...''

'' ሴትና ዶሮ ሳያብድ አይውልም ቂቂቂ! ...''

'' እሺ እሺ አንተም ሳቅብኝ... እናቴ ትመኑት አበዛኸው ! ''

'' እኔ እኮ አይደለሁም ያልኳችሁ። የድሮ ሰዎች ናቸው። ልቀጥል''

'' አሁንማ አንዴ ጀምረኸዋል ቀጥል እንጂ... ''

'' ሴትና ፈረስ እንደኩራ ውሃ እያደር ማነስ ? ''

'' እ.ሺ...''

'' ሴት የላከው ፣ ሞት አይፈራም ''

'' ምን ታየኛለህ_ ቀጥል! ''

'' ሴት የወደደ፣ ገሃነመ እሳት ወረደ ''

'' አባቴ ይመኑት፣ ይኸ ይኸ የሆሞዎች መፈክር ነው። ታዲያ ወንድ ልጅ ማንን ሊያፈቅር ኖሯል? ''

'' ቂቂቂ! ...እንጃ ለምን እንዲህ እንዳሉ የድሮ ሰዎች። ለማንኛውም ልቀጥል?...''

'' ቀጥል እንጂ አሁንማ ምን መቆሚያ አለው?''

'' ሴት አማት የመረዘው፣ ኮሶ ያነዘዘው ''

'' አማትም ሳትቀር በሴትነቷ? የሚገርም ነው ! ''

'' ሴት ካልወደደች ፣ ቋንጣ አትጠብስም ''

'' አንጀታችሁን ይጥበሰው ! ''

'' ቂቂቂ... ተይ እንጅ አትቆጪ... አስፈሬሽኝ ''

'' ፈት ዝላ ትፈራለች፣ አጥር ትመዛለች ''

http://ethioliberty.wordpress.com/

" አበጀች ምን ይጠበስ? "

" ታገሽ እንጂ ... ሴት ያመነ፣ ጉም የዘገነ "

" ወንዶች ናችኋ ታማኞቹ? ጉረኞች! "

" ሴት ያመጣው ጠብ አይበርድም "

" አትሳደብ..."

" እኔ አልሳደብም። የድሮ ሰዎች ናቸው ያሏችሁ። "

" እሺ ቀጥል..."

" ሴትና ዶሮ ዱር ሲሄዱ፣ ቢታቸውን ይከዱ"

" ሌላስ? "

" ሴት አግብተው ሴት ቢወልዱ የት አለ ንግዱ "

" ሌላስ ? "

" የሴት ሆዳም፣ ታማ አትኛም "

" ባለጌ !... "

" የሴት አመዳም፣ ያሀያ ሆዳም "

" ዝ ፍ ጥ !... "

" የሴት ክፉ ምላሰኛ፣ የጉረቤት ክፉ ምቀኛ "

" ቅሌታም !... "

" የሴት ምክር፣ የሾህ አጥር "

" በቃ የሴት ምሳሌ መወገዝ ብቻ ነው? ምን ዓይነት

http://ethioliberty.wordpress.com/

ሾቨኒስቶች ናችሁ? "

" እኔና የዛሬው ትውልድ እኮ አይደለንም የተረትነው ምነው ቅድም ነግሬሽ? ደሞም አንቺ ልዩ ሴት ነሽ። ጉዳዩ አንቺን አይመለከትሽምና አትበሳጪ... ፊትሽ እኮ ተለዋወጠ"

" አትሸልተኝ! ምኔ ነው ከሌሎች ሴቶች የሚለየኝ? ግን እንዴት ሁልህም ከሴት ተፈጥረህ እንዳልተፈጠርክ አስመስለህ ስለሴት እንዲት ቃል እንኳን በጎ አይወጣህም? በጣም የሚያስገርምና የሚያበሳጭ ድርጊት ነው ! "

" አይበዛም እንጂ ጥቂት ጥቂት በጎ ተረቶችም ተተርቶላችኋል እኮ! አይሾሽ አትበሳጪ ! "

" ለምሳሌ ምን ምን? "

" የሴት ለገሯ ባሏ "

" ታዲያ ይኸ ምንድነው? ተቀጥላነታችንን ነው የሚያሳየው "

" መልካም ሴት ለባሏ ዘውድ ናት "

" ይኸ እንኳን ይሻላል "

" የሴት ዘመናይ፣ የፊቷን እንጂ የጎኗን አታይ "

" ተመልሰህ እዚያው?... እናቴ ትሙት አሁንስ አበዛኸው !

" ይቅርታ! ... ሌላ እላለሁ ብዬ ነው_ ይኸን ያስቀደምኩት። ቂቂቂ!... የሴት ለጭር ወይዘሮ፣ የወንድ ለጭር ለውራ ዶሮ"

" እሰይ ! አንቺ ኩባያ እያልክ የምታፈዝብኝን መልሱን አገኘኸው ! ይኸ ጥሩ ምሳሌ ነው_ መጥኔ ላጭር ወንድ "

" ሴት ታውቅ፣ ለወንድ ያልቅ "

http://ethioliberty.wordpress.com/

“ ግሩም ነው ! ይኸን ይኸን የት አቆይተኸው ነው? ”

“ ታግሽ ብዬሻለሁ እኮ... ሴት ካልዋሸች፣ባሏን ትወልዳለች ሲባልስ?”

“ አልሰማሁም ፍቅርዬ... ይኸም ደግሞ ግሩም ነው ”

“ ሴትና መሬት የማይችሉት የለም ”

“ ይኸ በጣም በጣም ትክክል ነው ! ይኸን ሁሉ ስድብ ችዬ እስካሁን ካንተ ጋር መቆየቴ እራሱ ሁሉን ቻይ ለመሆናችን ምስክር ነው። እስቲ ቀጥል የኔ ወለላ...”

“ ተዚህ በላይ ደግ ደጉን አላውቅም ክፋ ክፋውን ልቀጥል? ”

“ አመጣኸው እንግዲህ ፣ የጭቃ ጅራፍክን... እንዴት መልካም መልካሙ ያልቅብሃል? ወንዶች ስትባሉ ትገርማላችሁ። አባቴ ይመኑት አለቅህም ቀጥል ደህና ደህናውን...”

“ አልቆብኛል...”

“ እንዴት እርግማኑ ሳያልቅ ምርቃቱ ያልቃል? አላምንህም ቀጥል ”

“ አልቆብኛል ስልሽ... ቢኖር ለማን ሰስቼው? ”

“ እሺ ግን አትርሳት!... እናቴ ትሙት እንዲያው ወንዶች ስትባሉ”

“ ተይ እንጂ አታልቅሺ!... እንዲያው ሴቶች ስትባሉ... ቂቂቂ...”

የ ል ብ ነ ገ ር

“ ምን ልብ አለህ? አለኝ እኮ!... ”
“ ማን? ”
“ ልብ የሌለው _ ”
“ ከልቡ? ”
“ እንኩት ! ”
“ የልብ ነገር ይገርማል ”
“ እንዴት? ”
“ ስለ ልብ ምን የማይባል አለ? ”
“ ምን ይባላል? ”
“ ልበ ሰፊ _ ነገር አለፈም ይባላል ”
“ ትክክል ! _ እኔም አንድ ልበልህ ”
“ እሺ ... ”
“ ልብ ሲያውቅ ጥርስ ከደመኛው ጋራ ይለታል ይባላል ”
“ ትክክል! ... ልብ ሲያውቅ _ ገንፎ ያንቅ እንዲሉ ”
“ ሌላም አለ _ ”
“ በል በለኛ _ ”
“ ልብ ሳይገዙ _ ነገር አያበዙ ”
“ እንዴት እንዴት? ”
“ ልብ ከጎንጅ _ ትምዛዙት ከደጅ እንዲሉ ነዋ ! ”

“ ትክክል! ... ልብ የሌላት ውሻ ማር ትቀላውጣለች ይባልም የለ ”

“ ትክክል!... ሌላም አለ ደግሞ ”

“ በል በለኛ _ ”

“ ልብ አንቅርትን ለማየት ይመኛል _ ይባል የለ? ”

“ እንዴታ! ከነጓዙ ስታየውማ የልብ ነገር ልብ ያማል ”

“ ጓዝም አለው ? ”

“ እንዴታ! ”

ልብ አልማ ታጥቆ አዛባ
ሱሪ አውልቆ ፈረስ ጋለባ
ራስ ተላጭቶ መለባ ... ሲባልም አልሰማህ ? ”

“ ሰምቻለሁ።። ተነምሳሌውም ፤ ልብ የሚገኝ በስልሳ _ ገንዘብ የሚገኝ በሠላሳ ይባላል ወንድምዬ!... ”

“ እንዲያ ነው ! _ ልብ ፋኛ _ ወይን አረኛ ይባልም የለ?

“ እውነት ነው _ ልብ እማይሆነው ምን አለ? ሁሉም በልብ ነው ”

“ ልብ አድርግ ይላሉ ”

“ ልብ በልስ ? ”

“ ልበ _ ቢስስ ? ”

“ ልብ ውልቅስ ? ”

“ ልብ ድክምስ ? ”

“ ልብ ጥፍት ”

http://ethioliberty.wordpress.com/

“ ልብ ቅልጥ ”

“ ልብ ስልም ”

“ ስልምልም _ ”

“ ልብ ፍስስ ”

“ ፍስስ ... ”

“ ወይ ልብ ሥራው ብዙ ”

“ አላድ አይሞላ ደሞዙ ”



የ አ ፍ ነ ገ ር

“ ክፍት አፍ አለኝ እኮ! ”
“ ማን? ”
“ አፈኛ- ”
“ አፉ ቢለጎም ይሆናላ ”
“ መቸ ቀንቶት ብለህ _ ይህ አንኮላ ”
“ ኋላስ? ”
“ ምህኛቱ ወዲህ ነው _ ”
“ ወዴት? ”
“ ተፈጥሮው ስድቡ ሁሉ የአፍ ነገር ነው ”
“ እንዴት? ”
“ እንጣ አባቱ! ... አፍ ለምዶበት ”
“ ያፍ ለመል እንዲሉ ማለት? ”
“ አፍ ዳገት አይፈራም ሲሉ ሰምቶ ”
“ እንዴት? ”
“ አፍ ታልተናገሩበት እዳሪ ነው ይባል የለ ”
“ እሱስ እርግጥ ነው። አፍ ያለው ጠፍ ይቆላል ”
“ አፉን ጠቅሞ ወርቁን ቅሞ _ ሲባልስ መቼ የዋዛ ”
“ ቢሆንም አፍ ያበዛ ፣ ጥበቡ ዋዛ እንዳይሆን ”
“ ቢሆንም አፍ ነገር ፣ ወይን አገር አያጣም ይባላል ”

http://ethioliberty.wordpress.com/

“ ቢሆንም አፍ ያለው ያግባሽ ክብት ያለው ነው ተረቱ ”
“ ምን የአፍ ነገር ብዙ ነው ”
“ እርግጥ መዘዙም የዚያኑ ያህል ”
“ አቆ ዝኛ፣ ልቡ ክነኛ እንዲሉ ”
“ እምን... አፍ ሲከፋ፣ ክሎሌ ይብሳል ”
“ በእርግጥ አፍ ሲያርፍ፣ ወዳጅንም ያማል ”
“ ቢሆንም አፍ ሲናገር ፣አፍንጫ ያሸሚጥጣል ”
“ አፍ ሲዋሽ፣ ሆድም ይታዘባል ”
“ በእርግጥ አፍ ሲናገር፣ ልብ ይንቃል ”
“ ቢሆንም አፈኛ ባቆ፣ ሀይለኛ በመዳቆ መመመካቱ አይቀርም”
“ ቢሆንም አፍና ቅብቅብ፣ ሁለዜም አያበሳም ይባላል ”
“ የለም አፍ ሲዶድ ክዕዳ፣ እግር ሲያድጥ ክአንጋዳ መዶሉ አይቀርም ”
“ እርግጥ በለፈለቆ፣ ባፍ ይጠቆ ”
“ አፍ አሳፈ፣ ያስክትላል ጥፈ”
“ አፈ ምላሴ ፣በደረቁ ይላሴ ”
“ የአፍ ዘመድ፣ ክዝለያም አይገድ እንዲሉ ”
“ እንዲያ እንዲያ ነው። አፍ የማይታማበት ምን አለ?”
“ ትንግርት እኮ ነው _ አይዋ አፍ በደግ አለመነሳቱ ”
“ ኧረ ወዲያ! እንኪን በደግ ሊነሳ በክፉ ስመ-ም በኖረ! ”
“ ሹል አፍ ! ሲባል ”
“ ኧረ ስንቱ ! ያፍ ነገር... ”



" የምሥራች!... የምሥራች አገኘሁልህ "

" ምስር ብይ ፍቅርዬ!... ምን አገኘሽልኝ? የጠፋብኝ ነገር ናሯል እንዴ አበባዬ? "

" እንዴታ!... የናንተን የወንዶችን ገጽታ የምታይበት መስታወት ጠፍቶብህ አልነበረም እንዴ? እሱን ነው ያገኘሁልህ ሆዴ...ቂቂቂ"

" ምን ዓይነት መስታወት? "

" ከመስታወትም መስታወት ወደል አሀያ የሚያሳክላችሁ "

" እንዴት? "

" ጆሮ ለባለቤቱ ባዳ ነው አለች እትዬ... እውነቷን ነው፡፡ የተባላችሁትን አልሰማህማ? ቂቂቂ "

" ምን ተባልን ወለላዬ? "

" ወንድና ወደል አሀያ አንድ ነው መባላችሁን... "

" ሌላስ ፍቅርዬ? ቂቂቂ "

" ወንድ ልጅ አንዴ አንቀባቱ! አንዴ አንደ አናቱም ተብሏል፡፡ "

" እና ምን ለማለት ነው? "

" ወንድ ልጅ እንላላቱም እንደ እናቱም የሚሆን እንጂ! ወንድ ልጅ ተወልዶ ካለሆን አንቀባቱ

አመልማሉ ስለት ይፍተል እንደናቱ እያላችሁ የምታላዝኑት አይሠራም ነው _ የሚላችሁ፡፡ "

" መልካም... ሌላስ የተባልነው አለ ሆዴ? "

" ሌላ ሌላውንማ አንተም ታውቀዋለህ፡፡ እራሳችሁን ከፍ ከፍ እያደረጋችሁ ከሰማየ ሰማያት ያመጠቃችሁበት ተረታችሁ ብዙ ነው፡፡ "

" ለምሳሌ? ቂቂቂ "

" ወንድ ልጅ ሰፈረሰ! ሴት ልጅ ለበርናሴ...

" ሌላስ አመዬ? "

" ወንድ ልጅ በተጎመበት! ሴት ልጅ ባገባችበት ዓይነቱ... "

" ቀጥይ ፍቅርዬ... ቀጥይ! "

" ያ ደሞ በቀደም እንዲህም ይባላል ያልከኝ ምን ነበር? "

" የቱ? የቱ ነው ሆዴ?... "

" ያ እንሂን ወንድና አንበሳ ምናምን ናቸው ያልከው_ "

" አሃ!... ወንድ ልጅ በበላበት! አንበሳ በለበረበት የሚባለው..."

" አምን!... ይኼ ይኼ ሁሉ የወንድን የበላይነት ለማንጸባረቅ የተረታችሁት አሮጌ የስብስቴ እምነታችሁ ገጽታ ነው፡፡ "

" ግን ግን ምን አናደደሽ? በቀደም ስለሴቶች ለንጉጋር እንደዚያ ብግን ብለሽ! በማሥቱ ለፍቺ ተጋብዝሽ... የድሮ ተረት መሆኑን አስረድቼሽ የኋላ የኋላ ተረጋጋሽ፡፡ ዛሬ ላገመኛ ንዴትን ምን አመጣው? "

" ለምን አልናደድ! ለምን አልበግን! ሁሉን በጎ ስንሙን

http://ethioliberty.wordpress.com/

ለራሳችሁ ስታደርጉ አታፍሩም? "

" እኛ የዛራዎቹ እኮ አይደለንም፤ የጥንቶቹ ናቸው ተራቶቹ፡ እናንተ ለእነሱ እፈሩ ነው የምትይኝ? "

" አዎና እፈሩ!... እፈሩ እስከወንድ ልጅ ዘረማንዘር... "

" ይሁና እንፈር ለጥንቶቹም እንፈርላቸው። ግና ወንድ አንደያዙት ነው ዓይነቱ ምላሌ እኮ ጥፋትም የለበት። "

" ሴትም እንደያዝዋት ነው የማይባልበትን ምክንያት ልትነግረኝ ትችላለህ? "

" አልችልም። "

" ምክኑስ? "

" ምክንያቱም እኔ አልተረትኩትማ... "

" ወንድ ሊበላ፤ የሴት ሌባ ዓይነቱስ ምላሌ ምን የሚሉት ነው? "

" እኔ እንጃ... ይልቅስ ወንድ ባለ በእለቱ፤ ሴት ባለች በዓመቱ ሲባል ሰምቻለሁ። ደስ አይልም። "

" በጣም በጣም እንጂ ፍቅርዬ... የማይጥም የግብዝ ተረት ነው። ባይሆን ወንድ ከዋለበት፤ ከብት ከተሰማራበት ዓይነቱ እንኪን ትንሽ በጣም ትንሽ ይሻል ይሆናል... "

" ለማንኛውም አይቻልም እንጂ ቢቻልና አንዳንዱን እሮጌ ተረትና ምላሌ ባዲስ በቀየርን በወደድኩ ነበር። ይቻል ይሆን? "

" ለምን አይቻልም? አስተሳሰባችንን ከቀየርን ተረቱም ተቀየረ ማለት መስሎኝ? "

http://ethioliberty.wordpress.com/

DFB

D AMH Lem
Lemma, Abera
Awchachgn 2002
hutl 1



03010856945001

ዋጋው ብር 5.50